# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 095 ታኅሣሥ 5 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









## ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ‘የአፍሪካ የላቀ አመራር’ ሽልማት ተበረከተላቸው

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በአረንጓዴ አሻራ ንቅናቄ ላሳዩት አመራር ‘የአፍሪካ የላቀ አመራር’ ሽልማት ተበረከተላቸው፡፡

“አፍሪካ፡ የዓለም አቀፍ ንቅናቄ አጣዳፊነት” በሚል መሪ ሃሳብ አሜሪካን አካዳሚ ኦፍ አቺቭመንት እና ግሎባል ሆፕ ኮአሊሽን የተሰኙት ተቋማት በዋሽንግተን ዲሲ በጋራ ባዘጋጁት ልዩ ዝግጅት ላይ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የአረንጓዴ አሻራ ንቅናቄን አስመልክቶ ላሳዩት አመራር ‘የአፍሪካ የላቀ አመራር’ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፣ በማኅበራዊ ትስስር ገፃቸው፤ ሽልማቱን መቀበላቸውን ገልፀው አሜሪካን አካዳሚ ኦፍ አቺቭመንት እና ግሎባል ሆፕ ኮአሊሽን

ጠቅላይ ሚኒስትር… ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ኢትዮጵያ በአረንጓዴ አሻራ መርሃግብር 25 ቢሊየን ችግኞችን መትከል ችላለች

## “ኢትዮጵያን ከአጎዋ ተጠቃሚነት ማገድ የሰብአዊ መብት ጥሰት ነው”

- አምባሳደር ጥሩነህ ዜና
የቀድሞ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽነር

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- አጎዋን እንደ ፖለቲካ መሳሪያ በመጠቀም ኢትዮጵያን ወደ ከአጎዋ ማገድ የሰብዓዊ መብት ጥሰት መሆኑን የቀድሞ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽነር አምባሳደር ጥሩነህ ዜና ተናገሩ፡፡

የቀድሞ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽነር አምባሳደር ጥሩነህ ዜና ከሰብዓዊ መብት ጋር ተያይዞ የአሜሪካ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ እያንጸባረቀ ያለውን አቋም አስመልክተው ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት “ገለልተኛ” የሰብዓዊ መብት መርማሪዎችን ካላስገባ አገሪቷ የአጎዋ ተጠቃሚ አትሆንም ተብሎ መነሳቱ የሰብዓዊ መብትን እንደ ፖለቲካ መሳሪያ መጠቀምን የሚያሳይ ነው፡፡

እንዲህ አይነት አካሄዶች፤ ለማንም ወገን እንደማይጠቅም የገለጹት አምባሳር ጥሩነህ፤ ኢትዮጵያ ከቀረጥ ነጻ ንግድ (አጎዋ) ተጠቃሚ እንዳትሆን የሚደረገው ተጽዕኖ በራሱ የሰብዓዊ መብት ጥሰትን የሚያሳይ ነው ብለዋል፡፡

አሜሪካ ኢትዮጵያን ከአፍሪካ የቀረጥ ነጻ ንግድ (አጎዋ) ተጠቃሚነቷ ላይ የጣለችውን እገዳ የምታነሳው የኢትዮጵያ መንግሥት ገለልተኛ የሰብዓዊ መብት መርማሪዎች በግጭት አካባቢዎች የሰብዓዊ መብት

“ኢትዮጵያን ከአጎዋ … ወደ ገጽ 4 ዞሯል













## ብልጽግና ፓርቲ በየደረጃው የሚገኙ አመራሮቹ ለአገራዊ ምክክር መድረኩ መሳካት ድጋፍ እንዲያደርጉ አሳሰበ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- “ለአካታች አገራዊ የምክክር መድረክ መሳካት ሁሉም የብልፅግና ፓርቲ አመራር አካላት የሚጠበቅባቸውን ሃላፊነት በአግባቡ መወጣት ይኖርባቸዋል ሲሉ የብልፅግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት

ብልጽግና ፓርቲ … ወደ ገጽ 4 ዞሯል







የንግድ፣ ቱሪዝምና ኢንቨስትመንት ዘርፉ እንዲነቃቃ በትኩረት እንደሚሰሩ ዲፕሎማቶች ተናገሩ

ገጽ 4

# ሙስናን የሚጸየፍ ትውልድ ለማፍራት ሁሉም ማህበረሰብ ሃላፊነቱን እንዲወጣ የሃይማኖት አባቶች አሳሰቡ

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- ሀገር አፍራሽና ትውልድ ገዳይ የሆነውን ሙስና የሚጸየፍ ትውልድ ለማፍራት ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ሃላፊነቱን እንዲወጣ የሃይማኖት አባቶቸ አሳሰቡ።

ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ቆይታ ያደረጉት የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ የሰላም ግንባታ መምሪያ ምክትል ኃላፊና የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት መምህር አዳነ ደቻሳ እንደተናገሩት፤ የደሃውን ጓዳ በማራቆትና አገር የሚያፈርሰውን ሙስናን መዋጋት የእያንዳንዱ ማህበረሰብ ኃላፊነት ነው።

አገርንና ሕዝብን በጽኑ የሚጎዳውን የሙስና ተግባር በትውልዱ ዘንድ እንዳይሰርጽ ለማድረግ የሃይማኖት ተቋማት፣ በጎ አድራጊ ድርጅቶች፣ መንግሥታዊና ማህበረሰብ አቀፍ ተቋምት በአጠቃላይም ሁሉም ሃላፊነት አለበት ብለዋል።

ሙስና በሃይማኖታዊ አስተምህሮም ፍጹም ተቀባይነት የሌለውና የተወገዘ ተግባር ነው ያሉት መምህር አዳነ ፤ ስለዚህ ሙስናን የሚቃወም ትውልድ ለማፍራት የሚደረገው ጥረት ቸል ሊባል እንደማይገባ ገልጸዋል።


ሼህ አብዱልሃሚድ አህመድ


መምህር አዳነ ደቻሳ

እንደ መምህር አዳነ ከሆነ፤ ሙስና በብዙዎች ዘንድ ጉቦ መስጠትና መቀበል ተደርጎ ቢታሰብም ሰው በአስተሳሰቡና በአገልግሎት አሰጣጡ ሙስናን ሊፈጽም ይችላል።

በመሆኑም ዘርፈብዙ መንገዶች ያሉትን የሙስና ተግባር ለመቀነስ ብሎም ለማጥፋት የተጀመረው እንቅስቃሴ የመንግሥት ሃላፊነት ብቻ ሳይሆን የሁሉም ህብረተሰብ ድርሻ መሆኑን ማስገንዘብ ይገባል ብለዋል።

መምህር አዳነ እንዳስታወቁት፤ ሙስናን መዋጋት የቤተሰብ አባላት የሚጀምርና በፍትህ ተቋማት ሊታገዝ የሚገባው ጉዳይ ነው። ቤተሰብ ልጆቹ ከሙስና የጸዱ ሆው እንዲያድጉ ማድረግ አለባቸው።

በአንጻሩ የፍትህ ተቋማት ደግሞ ሕጉን ተላልፈው የሚጓዙትን በአግባቡ በመቅጣት ኃላፊነታቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል ብለዋል።

የኢትዮጵያ እስልምና ጠቅላይ ምክር ቤት ሥራ አስፈጻሚ አባልና የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ምክትል ቦርድ ሰብሳቢ ሼህ አብዱልሐሚድ አሕመድ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ የሰሜኑን ጦርነት በስምምነት እንዲያበቃ ካደረገች በኋላ በአንድነት ሙስናን ለመቀነስ የጀመረችው እንቅስቃሴ የሚበረታታ ነው።

በዚህ ጥረት ተሳታፊ መሆንና ከሙስና ታቅቦ መቆየት መልካም ነው ያሉት ሼህ አብዱልሀሚድ፤ የእምነት ተቋማት ሙስናን ከማውገዝ አንጻር ሰፊ ሚናን መጫወት ቢኖርባቸውም ይህን ሲያደርጉ እምብዛም አይስተዋሉም ብለዋል።

ስለዚህ የእምነት ተቋማት ተከታዮቻቸውን የሙስናን አጸያፊነት ለተከታዮቻቸው ማስተማር እንደሚኖርባቸው ጠቁመዋል።

እንደ ሼህ አብዱልሐሚድ ገለፃ፤ በሙስና ተግባር ተሳታፊ የሆነ ሰው ሀገርን የመምራት አቅም አይኖረውም። ማንኛውም መሪ የሚያገኘውን ገቢ ከየት እንዳመጣውና ምን እንደሰራ መታወቅ አለበት። ይህም አገርን ከሙስና አቅቦ ለመቆየት ያስችላል።

ብረተሰቡን ያማረሩ የሙስና ተሳታፊ ቡድኖችንና ግለሰቦችን በማጋለጥ ለአገር ዕድገት ዘብ እንዲቆም የሃይማኖት አባቶቹ ጥሪ አቅርበዋል።

# ከታህሳስ 13 ጀምሮ በአገር አቀፍ ደረጃ የኩፍኝ ክትባት ይሰጣል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኩፍኝ ክትባት በሀገር አቀፍ ደረጃ ከፊታችን ታህሣስ 13 ቀን ጀምሮ የሚሰጥ በመሆኑ እስከ 5 ዓመት የእድሜ ክልል ያሉ ህፃናት እንዲከተቡ ጥሪ ቀረበ።

የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የኩፍኝ በሽታ መድኃኒት ክትባት ማሠራጨቱን በመድኃኒት ክምችት አያያዝ አስተዳደር የክትባት መድኃኒት ተጠሪ አቶ ሀብታሙ አለማየሁ ገልጸዋል።

የክትባት መድኃኒቱ በመላው የኢትዮጵያ ክልሎች የሚካሄድ ሲሆን ፥ በዚህም 16 ሚዮዮን 298 ሺህ በላይ ሕፃናትን ለመከተብ ዕቅድ መያዙን ተጠቁሟል።

ክትባቱ ከታህሣስ 13 ቀን ጀምሮ እንደሚሠጥና እስከ 5 ዓመት የእድሜ ክልል ያሉ ሕፃናት እንዲከተቡ ጥሪ መቅረቡን ከአገልግሎቱ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።



የኩፍኝ በሽታ በትንፋሽ ከሠው ወደ ሠው በከፍተኛ ፍጥነት የሚተላለፍ መሆኑ ታውቋል። ይህ በሽታም ሕፃናትን እስከ ሞት ሊያደርስ የሚችል በመሆኑ ማህበረሠቡ ይህንን በመገንዘብ ሕፃናቱን በወቅቱ እንዲያስከትብ አገልግሎቱ ጥሪ አቅርቧል።

በአብዛኛው ሕጻናትን የሚያጠቃው የኩፍኝ በሽታ ተላላፊ በሽታ ሲሆን ተገቢው የሕክምና ክትትል ከተደረገ መዳን ይቻላል። ይሁንና በበሽታው ላለመጠቃት አስቀድሞ ክትባት መውሰድ ይመከራል።

የኩፍኝ በሽታ ተገቢውን የህክምና ክትትል ካላገኘ ከመግደል ጀምሮ ዘላቂ ለሆነ የአዕምሮ ጉዳት፣ ለሳንባ ምች፣ ያለጊዜው ጽንስ መውለድ፣ ለመስማት ችግር እና ለሌሎች ጉዳቶች የሚዳርግ በሽታ መሆኑን የዓለም ጤና ድርጅት ገልጿል።

የኩፍኝ በሽታ የመከላከያ ክትባት ሕፃናት በሽታውን የመከላከል አቅማቸው እንዲጨምር ብሎም በሌላ በሽታ እንዳይያዙ እና ጤነኛ እንዲሆኑ የሚያግዝ ነው ተብሏል።

ከዚህ ባለፈም የኩፍኝ በሽታን ሙሉ በሙሉ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለማጥፋት የተያዘውን ዘመቻ ውጤታማ ለማድረግ የክትባት መርሀ ግብሩ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

የኩፍኝ በሽታ ሕፃናትን ለሞት የሚዳርግ ብሎም ለከፍተኛ የአካል ጉዳት የሚያደርስ በሽታ መሆኑ ይታወቃል።

# የሌማት ትሩፋት በምግብ ራስን ለመቻል ከሚደረገው እንቅስቃሴ ባሻገር ሰፊ የስራ እድል የሚፈጥር መሆኑ ተገለጸ

## - ከአንድ ላም በቀን እስከ 15 ሊትር ወተት ለማግኘት ይሰራል

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- የወተት፣ ዶሮና፣ የማር ምርትን እንደ ሀገር ለማሻሻል የተጀመረው የሌማት ትሩፋት በምግብና በሥነምግብ ራስን ለመቻል ከሚኖረው አስተዋጽኦ ባሻገር ሰፊ የስራ እድል የሚፈጥር መሆኑ ተገለጸ፡፡ ከአንድ ላም በቀን እስከ 15 ሊትር ወተት ለማግኘት እየተሰራ ነው፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የእንስሳት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ፍቅሩ ረጋሳ ከፋና ቴሌቭዥን ጋር በነበራቸው ቆይታ፣ የሌማት ትሩፋት ከአረንጓዴ አሻራና የበጋ ስንዴ መስኖ አገራዊ ንቅናቄዎች የቀጠለና በሀገራችን ካላት ጸጋ አንዱ ከሆነው ከእንስሳት ዘርፍ በምግብና በሥነምግብ ራስን ለመቻልና መአድ እንዲሞላ የማድረግ ፕሮግራም መሆኑን አብራርተዋል።

በፕሮግራሙ በየክልሉ የወተት፣ የዶሮ፣ የማር መንደሮች ይቋቋማሉ፤ በየመንደሩም ምን ያህል አባወራዎች እንዳሉ ጭምር ጥናት ተደርጎ ለራሱ የሚያመርተውንና የሚተርፈውን ወደ ሌሎች መንደር ተዋጽኦዎች ማቅረብ የሚያስችል አሰራር መኖሩንም ጠቁመዋል።

ፕሮግራሙ ከውጭ የሚገባውን የእንስሳት ምርት በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካትና ወደ ውጭ የሚላከውን የእንስሳት ተዋጽኦ ለማሳደግ ያለመ ነው ያሉት ዶክተር ፍቅሩ፤ የእንስሳቱ ዘርፍ የሚፈጥረውን ሰፊ የስራ እድል በመጠቀም ምርትና ምርታማነቱን በማስፋት ሰፊ የስራ ዕድል መፍጠር ማስቻል ላይ ያተኮረ ንቅናቄ መሆኑንም አስረድተዋል።

ከሀገራችን የወተት ምርት ተገቢውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ማግኘት አለመቻሉ የሚያስቆጭ ነው ያሉት ዶክተር ፍቅሩ፤ ናሚቢያ 2 ነጥብ 9 ሚሊዮን የቀንድ ከብት ይዛ 300 ሚሊየን ዶላር ዓመታዊ ገቢ ታገኛለች። ኢትዮጵያ ግን በርካታ እንስሳት ይዛ የምታገኘው አመርቂ አይደለም ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያ የመኖ አቅርቦት፣ የዝርያ ማሻሻል ሁኔታ፣ የወተት አያያዝ ከኬንያ እና ሩዋንዳ ከመሳሰሉት አጎራባች አገራት ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ ነው። ይህም ኢትዮጵያ በዓመት የምታገኘው የላም ወተት ዝቅተኛ አድርጎታል። በመሆኑም በቴክኖሎጂ በመደገፍና ዝርያቸው የተሻሻሉ የወተት ላም እርባታ በመጠቀም ምርታማነታቸውን ማሻሻል እንደሚገባ አመላክተዋል።

በኢትዮጵ 15 ሚሊዮን የወተት ላም በማዳቀል የተሻሻሉ ጊደሮችን ለማግኘት የሚያስችል ጥናት መደረጉንም ገልጸዋል። በዚህም ከአንድ ላም በአማካይ በቀን ከ 10 እስከ 15 ሊትር ወተት ወደ ማግኘት ደረጃ ማድረስና ከሌሎች አገራትም የበለጠ የወተት ምርት ማግኘት የሚቻል መሆኑንም አመላክተዋል።

የግመል ወተት በተመለከተ የተሻለ የግመል መኖ አቅርቦት በማመቻቸት ብቻ ከጎረቤት አገራት በአንጻራዊነት አሁን ከሚገኝበት የተሻለ የግመል ወተት ምርትን ይበልጥ መጨመር በሚቻልበት የጥናት ግኝቶች መኖራቸውንም ጠቁመዋል።

ዶክተር ፍቅሩ የማር ምርትን በተመለከተ እንደገለጹት፣ እንደ ሀገር ሰባት ሚሊዮን የንብ መንጋ ቢኖርም 90 በመቶ በባህላዊ ቀፎ የሚገኙ ናቸው። በባህላዊ መንገድ በአንድ ቀፎ በአማካይ 10 ኪሎ ማር ይገኛል። ነገር ግን በዘመናዊ አንድ ቀፎ በአማካይ 30 ኪሎ ማር ማግኘት ይቻላል።

በባህላዊ ዘዴ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ በመቁረጥ 10 ኪሎ የሚገኘውን የማር ምርት ዘመናዊ ቀፎ በመጠቀምና የተሻሻለ የአበባ መኖ በማቅረብ በአንድ ቀፎ 30 ኪሎ ማር ማግኘትና በዓመት እስከ አራት ጊዜ መቁረጥ የሚያስችል መሆኑንም ጠቁመዋል።

ስለዚህም ባህላዊውን ወደ ዘመናዊ ቀፎ በመቀየር ብቻ ከአንድ ቀፎ የሚገኘውን የማር ምርት ወደ 20 ኪሎ ወይም በ200 በመቶ በማሳደግ ይቻላል። በሀገራዊ ፕሮግራሙ የማር ምርትን ወደ ሁሉም አህጉር ለመላክ በሚያስችል ደረጃ በትኩረት ይሰራል ብለዋል።

ሁሉም ክልሎች ለዶሮ እርባታ፣ ለላም ወተት እንዲሁም ለማር ምርት ያለውን አመቺነት በማየት አስተባባሪ ኮሚቴና እና ቴክኒካል ኮሚቴ በማቋቋም በየዞን፣ ወረዳ እና በቀበሌ እና በቤተሰብ ደረጃ በማውረድ ሥራ ላይ ማዋል እንደሚገባም አመላክተዋል።

የእንስሳት ልማት እንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር አስራት ጤራ በበኩላቸው፣ ከበጋ ስንዴ እና አረንጓዴ አሻራ ሀገራዊ አጀንዳዎች የቀጠለው የሌማት ትሩፋት ፕሮግራም ሀገራችን የምግብ፣ የሥነምግብ፣ የስራ እድል፣ የውጭ ገቢ እና ሌሎችንም እምርታዎች ሊያስገኝ የሚችል ነው ብለዋል። በየደረጃው የሚገኘው አመራር በአንድ ሃሳብ በቀላሉ ሊያሳካው የሚችለው ሀገራዊ ፕሮግራም እንደሆነም ተናግረዋል።

ዶ/ር አስራት ጤራ እንዳብራሩት በ2021 ስታቲስቲክስ መረጃ መሰረት በሀገራችን አንድ ሀገረሰብ ላም በቀን በአማካይ 1 ነጥብ 428 ሊትር ወተት ስትሰጥ የተሻሻለ ዝርያ እስከ 15 ሊትር ወተት መስጠት ይችላል። ዝርያቸው የተሻሻለ አንድ የወተት ላም 15 የሀገረሰብ ላሞች የሚያመርቱት ያህል ወተት ያመርታሉ። 15 የሀገረሰብ የወተት ላሞች የሚመገቡት መኖ፣ የሚይዙት ቦታ፣ በአካባቢ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ሰፊ መሆኑ ጠቁመው፤ ነገር ግን የመኖ እጥረትን፣ የአየር ፀባይን የመቋቋም አዎንታዊ ጎን አላቸው። በመሆኑም ጥራት ላይ በማተኮርና የወተት ምርት በማሻሻል ከእጥረት ጋር ተያይዞ ኢትዮጵያ ከውጭ ለማስገባት 25 ሚሊዮን ዶላር በላይ ዓመታዊ ወጪ ማስቀረት ተገቢ መሆኑን አመላክተዋል።

ለአርሶ አደሩ የተሻሻሉ ዝርያዎችን በመጠቀም የተሻለ ምርት በማግኘት የቤተሰብ የምግብ ዋስትና ከማረጋገጥ አልፎም ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታውም ከፍ ያለ መሆኑን አስገንዝበዋል።

በዚህ ዓመትም ከ2 ሚሊዮን ዶዝ በላይ የተሻሻሉ ጊደሮች አባላዘር ለማምረት መታቀዱን ያመላከቱት ዶክተር አስራት፣ በዚህ ሀገራዊ መርሃ ግብር እስከ 14 ሚሊዮን ዶዝ አባለዘር በማምረት ከ5 ነጥብ 75 ሚሊዮን በላይ ዝርያቸው የተሻሻሉ ላሞች እንዲያረግዙ ይደረጋል። የተሻሻሉ የወተት ላም ዝርያዎችን የሚያዳቅሉ ቴክኒሻኖችን በማሰልጠን፣ ሎጂስቲክስ በማሟላት ከፍተኛ እምርታ ማምጣት የሚቻል መሆኑንም አመላክተዋል።

በሀገራዊ የሌማት ትሩፋት ፕሮግራሙ አርሶ አደሩም፣ አርብቶ አደሩም የተሻለ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚያገኝበትና ፍላጎት ያሳየበት ነው ብለዋል። በኦሮሚያ፣ በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ትኩረት፣ ፍጥነት እና ስኬሉን በመጨመር በስፋት መጀመሩን ገልጸዋል። በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት በየጊዜው ክትትል ሊደረግና ሊተገበር የሚገባ መሆኑንም ጠቁመዋል።

# በአገራችን ሰፊ የቀርከሃ ሀብት ቢኖርም በሚገባው ልክ ጥቅም ላይ እንዳልዋለ ተጠቆመ

**በኃይሉ አበራ**



አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ከፍተኛ የቀርከሃ ሀብት ቢኖራትም ከዘርፉ ብዙ እንዳልተጠቀመች የዘርፉ ባለሙያ ገለጹ፡፡ የቀርከሃ ሀብት ትኩረት ተሰጥቶች ሊለማና ለሀገር ምጣኔ ሀብት ሊውል እንደሚገባም ጠቁመዋል።

በቤኒሻንጉል ክልል ግብርና ቢሮ የብዘሃ ሕይወት ልማት እና ጥበቃ አጠቃቀም ዳይሬክቶሬት የእፅዋት ጥበቃ ባለሙያ አቶ ጀማል ዑመር ሆጀሌ፣ በክልሉ ከሚገኙ እምቅ የተፈጥሮ ሀብቶች አንዱ የሆነው የቀርከሃ ሀብት በትኩረት ሊሰራበትና ሊለማ እንደሚገባ አመላክተዋል።

ዳይሬክቶሬቱም የቀርከሃ ሀብትን ጨምሮ በክልሉ የሚገኘውን እምቅ ሀብት ለመለየት፣ ለማልማትና ስለአጠቃቀሙ ለማስገንዘብ በቅርቡ የተቋቋመ ነው ብለዋል።

አቶ ጀማል በአሶሳ ወረዳ ላይ ብቻ በተደረገ ጥናት ከ77 ሺህ ሄክታር በላይ ጥቅጥቅ የቆላማ አካባቢ ቀርከሃ መኖሩን ጠቅሰው አሁን ሀብቱ እየተመናመነና በተገቢው እየተጠበቀ አለመሆኑንም አመላክተዋል።

ቀርከሃ ለዙምባራ ሙዚቃ መሳሪያዎች ሥራ፣ ለምግብነት፣ ለእንስሳት መኖ፣ ለመድሃኒትነት፣ ለውሃ ማጣሪያነት፣ ለቤት ግድግዳና ጣሪያ መስሪያ፣ ለፈርኒቸር፣ ለተለያዩ የእርሻ መሳሪያዎች አገልግሎት ጨምሮ ከ2500 በላይ ጠቀሜታ እንዳለው በጥናት መመዝገቡንም ጠቁመዋል።

በክልሉ የሚገኘው የቆላ ቀርከሃ ውስጡ ድፍን የሆነ በዘር የሚራባ ሲሆን ከአንድ ዓመት እስከ ሁለት ዓመት እድሜ ያሉትን ቆርጦ በመትከል ማባዛት የሚቻል መሆኑንም አስረድተዋል።

እድሜው በጨመረ ቁጥር ጥንካሬው የሚጨምር መሆኑን የገለጹት አቶ ጀማል፣ በቻይና ለህንጻ ግንባታ ብረትን በመተካት እስከ 20 ፎቅ ድረስ የሚሰራበት ሁኔታ መኖሩንም ገልጸዋል።

ቀርከሃ በክልሉ በአምስቱም ብሔረሰቦች ለምግብነት የሚውል ሲሆን በውስጡ የሚገኘው ፎሊክ አሲድ የተባለ ንጥረ ነገር ለተለያዩ ባህላዊ ህክምናዎች እንደሚያገለግልም ጠቅሰዋል፡፡

የቆላ ቀርከሃ ለአርባ ዓመት ፍሬ የሚሰጥ ሲሆን አዲሱ ተክልም በተመሳሳይ ኡደት አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑን አብራርተዋል። እስከ 40 ሜትር ቁመት እና ሁለት ሜትር የጎን ስፋት ያላቸው የሃይላንድ ባምቡ የሚባሉ ቻይና አካባቢ የሚገኙን ጨምሮ ከ1200 በላይ ዝርያዎች እንዳሉት ጥናቶች የሚጠቁሙ መሆኑንም ገልጸዋል። ቀርከሃ አርባ ዓመት ሙሉ ምርት የሚሰጥ በመሆኑ አዋጭነት ያለው መሆኑን አመላክተዋል።

እንደ አቶ ጀማል ገለጻ፤ ቀርከሃ በክልሉ ለሚገኘው ከፍተኛ የማር ሀብት ዘመናዊ የንብ ቀፎ መሥሪያነት ጨምሮ ለበርካታ የፈርኒቸር ስራዎች አገልግሎትም ይውላል።

ነገር ግን አሁን አሁን ላይ በእርሻ መስፋፋት፣ በሰደድ እሳትና በተለያዩ አደጋዎችና በግንዛቤ ማጣት ሀብቱ እየወደመ ነው ያሉት አቶ ጀማል፤ ይህንን በማገም በኩል ትኩረት እንዲሰጠውም አሳስበዋል።

በክልሉ የቀርከሃ ሀብት ላይ በማኑፋክቸሪንግ ደረጃ እንቅስቃሴ ጀምሮ የነበረው “ባምቡ ስታር” የተባለ ድርጅት አሁን ስራ ያቆመ መሆኑንም ጠቁመዋል።

በሀገራችን በከፍተኛ መጠን ለሚገኘው የቀርከሃ ሀብት ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ወደ ኢኮኖሚያዊ አቅም በመቀየር የሀገራችንን ምጣኔ ሀብት ማሳደግ እንደሚገባም ጠቁመዋል።

ጥናቶች እንደሚጠቁሙት በአፍሪካ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር የሚሸፍኑ 43 የባምቡ ዝርያዎች ይገኛሉ። በሀገራችን የቆላማና ደጋማ ቀርከሃ ዓይነት በብዛት ሲገኝ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የቆላማ ቀርከሃ በብዛት የሚገኝበት ነው።



# ባለሥልጣኑ በግንባታ ዘርፍ የሚስተዋሉ ብልሹ አሰራሮችን ለመቅረፍ እየሰራ ነው

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በግንባታ ዘርፍ የሚስተዋሉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮች ለመቅረፍ እየተሰራ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ፍቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አስታወቀ፡፡

ባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ስጦታው አካለ እንደገለጹት፣ ግንባታ ዘርፉ ለሙስናና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ ከሆኑት ዘርፎች አንዱ ሲሆን በዘርፉ የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አስራርንና ለመቅረፍ እየተሰራ ነው፡፡

ባለሥልጣኑ ለዓመታት ሲጠቀምባቸው የነበሩት መመሪያዎች፣ አሰራሮች፣ የሕግ ማዕቀፎች ለሙስናና ብልሹ አስራር ምቹ እንደነበሩ የጠቀሱት ኢንጂነር ስጦታው፤ ለብልሹ አሰራሮች ተጋላጭ ለሆኑት የሕግ ማዕቀፎችና አሰራሮች ማስተካከያ የማዘጋጀት ሥራም ተሰርቷል ብለዋል፡፡

ሙስና ዴሞክራሲ እንዳይሰፍን እንቅፋት እንደነበረና የአገርን ኢኮኖሚ እንዲጎዳ ከማድረጉም በላይ እንደ አገር ሰላምና መረጋጋት እንዳይኖር ሰፊ አስተዋፅኦ ማበርከቱን የተናገሩት ዋና ዳይሬክተሩ፤ አሁን ግን ሙስናን የመከላከል ሥራ ላይ በትኩረት እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡

ሙስናን ለመከላከል አገራችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ሕግ ከማርቀቅ ጀምሮ እየተሳተፈች የራሷን አስተዋፅኦ ስታደርግ ቆይታለችም ሲሉ የተናገሩት ዋና ዳይሬክተሩ፣ በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችና ማነቆዎች በመለየት የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱን አመልክተዋል፡፡

ሙስናን የሚታገልና የሚፀየፍ ጥቂት ሰዎች ብቻ ሳይሆን ሁሉም ዜጋ ከሃሳቡ ጀምሮ ተግባሩን በአጸያፊነት በመፈረጅ ድርጊቱን ለመከላከል ርብርብ ሊያደርግ ይገባል ያሉት ኢንጂነር ስጦታው፤ ለአገራችን እድገትና ብልፅግና አሻራችንን የምናሳርፈው በጥሩ ሥነ-ምግባር ማገልገል ሲቻል በመሆኑ ሁሉም የሙስና ማድረቂያ ዘዴዎችን አውቆ ሊተገብር ይገባል ብለዋል፡፡

በተቋሙ ሙስናንና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል መመሪያና ማንዋሎችን በማሻሻል ተግባራዊ መደረጉንም ተናግረዋል፡፡

በዘርፉ በተደረጉት ማሻሻያዎችም ሲስተዋሉ የነበሩት የሌብነትና የብልሹ አሰራሮችን በመቅረፍና በመታገል በየደረጃው የተጠያቂነት ሥርዓት ይሰፍናል ብለዋል፡፡

የተጠያቂነት ሥርዓትን እንደ ተቋም አጠናክሮ ማስቀጠል የሚቻልበትን ስልትና አሰራር እንደሚዘረጋ ያነሱት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በቀጣይነትም ብልሹ አሰራርን ለመቀነስ አመለካከት ላይ ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሰራም ተናግረዋል፡፡



አቶ ዘመድኩን አበበ የኢትዮጵያ ጤና መድን አገልግሎት የኮሙኒዩኬሽን ዳይሬክተር



ወይዘሮ አልማዝ ደጉ



ወይዘሮ ሽምሳ ሱራች



አላዛር አደፍርስ

# የጤና መድህን አገልግሎት ከዘርፈብዙ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግር እንደታደጋቸው ተገልጋዮች ተናገሩ

## - ከ9 ነጥብ 8 ሚሊዮን በላይ አባወራዎችና እማወራዎች ተጠቃሚ ሆነዋል

**ልጅአለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የማህበረሰብ አቀፍ ጤና አገልግሎት ከዘርፈብዙ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች እንደታደጋቸው ተገልጋዮች ተናገሩ። አገልግሎቱ በገንዘብ እጦት ምክንያት ሕይወታቸው አደጋ ላይ ከመውደቅና ሀብት ንብረታቸውን ከመሸጥ እንደታደጋቸውም ጠቁመዋል። እስካሁን ድረስ በአገር አቀፍ ደረጃ ከ9 ነጥብ 8 ሚሊዮን በላይ አባወራና እማወራ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆናቸውም ታውቋል።

የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድን አገልግሎት የጎላ ጠቀሜታ እንዳለውና ማህበረሰቡ በተለይም በኢ-መደበኛ ስራ ዘርፍ ውስጥ ለምንተዳደር ሰዎች የጤና ችግር ቢያጋጥመን የገንዘብ እጥረት ሳያሳስበን ህክምና ማግኘታችን ማህበራዊ ሕይወታችን በአግባቡ እንድንመራ አስችሎናል ሲሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አስተያየታቸውን የሰጡ ተገልጋዮች ተናግረዋል።

አስተያየት ከሰጡት ተገልጋዮች መካከል ወይዘሮ አልማዝ ደጉ የማህረሰብ አቀፍ ጤና መድን ለሕይወታችን ትልቅ ዋስትና መሆኑን ገልጸዋል። አገልግሎቱን መጠቀም የጀመሩት ከአራት ዓመት በፊት መሆኑን ያስታወሱት ወይዘሮዋ፤ ይህ ነው የሚባል ገቢ ባይኖረኝም በጤና መድህን አገልግሎት ተጠቃሚ መሆኔ ለህክምና ወጪ ሳያስጨንቀኝ እስከ የካቲት 12 ሆስፒታል ሄጄ ቀዶ ጥገና (ኦፕሬሽን) ሆኛለው ይላሉ።

አገልግሎቱም ከብዙ ችግር ገፈት ቀማሽ ከመሆን ታድጎኛል ያሉት ወይዘሮዋ፤ የአባልነት መታወቂያ ወስዶ በአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን አስፈላጊና ጠቃሚ ነው ብለዋል።

ሕመምና አደጋ ድንገት የሚያጋጥም በመሆኑ ስንታመም ምንም አይነት ገንዘብ ሳንይዝ በመታወቂያ ብቻ በማሳየት መታከም መቻል በጣም ትልቅ ነገር ነው ሲል የተናገረው ደግሞ ወጣት አላዛር አደፍርስ ነው። የጤና መድህን አገልግሎት በተለይ አነስተኛ ገቢ ላለው ህብረተሰብ ጥቅሙ ፈርጀ ብዙ መሆኑን ገልጾ፤ የዚህ አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አይደለም ብሏል።

ወይዘሮ ሽምሳ ሱራች በበኩላቸው አገልግሎቱ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው ጠቁመው፤ በገንዘብና በህክምና እጦት ለስቃይና እንግልት ጠና ሲልም ለሞት ከመዳረግ ታድጎናል ሲሉ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ጤና መድን አገልግሎት የኮምኒዩኬሽን ዳይሬክተር አቶ ዘመድኩን አበበ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት ማብራሪያ አገልግሎቱ ባህላዊ ሕክምናና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ከማስቀረት ባሻገር የሴቶችና ሕጻናት በራስ መተማመንን ያጎለበተ ነው።

የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድን አገልግሎት ያለው ጠቀሜታ ዘርፈ ብዙ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ የህክምና ተጠቃሚነት በተጨማሪ የኢትዮጵያዊነት መረዳዳትና መተሳሰብ ያዳበረ መንግሥታዊ መዋቅር መሆኑን ገልጸዋል።

በአሁኑ ጊዜ አገልግሎቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ ስራው በጥሩ ሁኔታ እየተሳለጠ መሆኑን ጠቅሰው፤ ማንኛውም አባል የሆነ ሰው ምንም ዓይነት ሰዓትና ቦታ ሳይገድበው ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ ሪፈራል ሆስፒታል ድረስ ሕጋዊ መንገድ ተከትሎ የህክምና አገልግሎት ማግኘት እንደሚችል ገልጸዋል።

አባል ሆነው ዓመታዊ ክፍያውን መክፈል ለማይችሉ ሰዎችም ክፍያው በመንግሥት ድጎማና በተለያዩ በጎ ፈቃደኛ ግለሰቦችና ድርጅቶች እንደሚሸፈን ተናግረዋል።

የመድሃኒት እጥረት አለ ፤ አልፎ አልፎም መድሃኒት እያለ የለም የሚባልበት ጊዜ አለ ሲሉ ተጠቃሚዎች ቅሬታ ያቀርባሉ ፤ ለዚህ ጥያቄ እርስዎ ምን ምላሽ አልዎት ብለናቸው በጣም ውስን በሆኑ ሥነ-ምግባር በጎደላቸው አካላት እንደዚህ ዓይነት እኩይ ተግባር የሚፈጽሙ አሉ። ነገር ግን በሀገር አቀፍ ደረጃ የመድሃኒት አቅርቦት ችግር ስላለ በሁሉም ታካሚዎች የሚስተዋል እንጂ ጤና መድን ተጠቃሚዎች ላይ ብቻ የሚከሰት አይደለም። ችግሩን ለመቅረፍ የመፍትሔ አቅጣጫዎች አስቀምጠን ወደ ተግባር እየገባን ነው ብለዋል።

ተቋሙ የታለመለትን ግብ እንዳያሳካም በማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን አገልግሎት ያለው የግንዛቤ ችግር፣ የሰላም መደፍረስ፣ ሰዎች ለተቋሙ የሚሰጡት መጥፎ ምልከታና የፋይናንስ እጥረት ለስራቸው መሰናክል ሆኖባቸው እንደነበር ገልጸዋል። ነገር ግን እነዚህ ችግሮች የነበሩ ቢሆንም ለወደፊት ሙሉ በሙሉ ተቀርፈው ደረጃችን ከፍ በማድረግ ሁሉም ዜጋ የተቋሙ አባል በመሆን ከሀገር አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ አባሉ ህክምና ማግኘት የሚችልበት ሁኔታ እንፈጥራለን ብለን እየሰራን እንገኛለን ሲሉ ተናግረዋል።

እስካሁን ድረስ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከ9 ነጥብ 8 ሚሊዮን በላይ አባወራና እማወራ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆናቸውን ገልጸው፤ በቤተሰብ ደረጃ ሲታይ ደግሞ ከ45 ሚሊዮን ሰዎች በላይ ተጠቃሚ ማድረጉን አስታውቀዋል።

# የንግድ፣ ቱሪዝምና ኢንቨስትመንት ዘርፉ እንዲነቃቃ በትኩረት እንደሚሰሩ ዲፕሎማቶች ተናገሩ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- በንግድ፣ በቱሪዝምና በኢንቨስትመንት ዘርፉ ያለውን መልካም አጋጣሚ ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በማስረዳት የቱሪስት ፍሰትና የወጪ ንግድ ለመመለስና ከነበረውም እንዲልቅ ትኩረት ሰጥተው እንደሚሰሩ በኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ዙሪያ ስልጠናና የተልዕኮ አቅጣጫ የወሰዱ ዲፕሎማቶች ገለጹ።

በኬንያ ናይሮቢ ያገለገሉትና አሁን በዋናው ሚኒስቴር መስሪያ ቤት የተመደቡት ዶክተር ዘሩባቤል ጌታቸው፤ በጎንደር የጎርጎራ ፕሮጀክትን፣ በሰሜን ጎንደር የቱሪስት መስህቦችን በጎበኙበት ወቅት የኮቪድ ክስተትና በአካባቢው የነበረው የጸጥታ ሁኔታ የቱሪዝም ዘርፉን እንደጎዳው መመልከታቸውን ጠቁመዋል።

በቢሾፍቱ እና አካባቢዎቹ እንዲሁም በደብረብርሃን የሚገኙ የኢንዱስትሪ መንደሮቹ ምልከታቸው አንዳንድ የተናጠል ማዕቀቦች ዘርፉን እንደጎዳው በዚህ ምክንያት በግማሽ አቅማቸው እንዲሰሩ የተገደዱ ፋብሪካዎች መኖራቸውን መታዘባቸውን ተናግረዋል።

የሰላም ስምምነቱ አካባቢዎቹ ለቱሪዝም እና ለንግድ ምቹ እንዲሆኑ ማስቻሉን በምልከታቸው ማረጋገጥ እንደቻሉና ትኩረት ሰጥተው በመስራት የተጣለባቸውን ሃላፊነት እንደሚወጡም ጠቅሰዋል። ሰሞኑን በቱሪዝም እንዲሁም በአምራች ዘርፉ ያደረጓቸው ጉብኝቶች ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳላቸውም አረጋግጠዋል።

በአንድ ገበያ መዳረሻ ላይ መመስረት ብቻ ሳይሆን ሌሎች እድሎችን በመመልከት ሰፊ የገበያ ዕድል እንዲኖር በማድረግ የተቀዛቀዘው የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ እንዲነቃቃ ሃላፊነታችንን መወጣት አለብን ነው ያሉት።

ዲፕሎማሲ ለኢትዮጵያ ዋነኛ ምሰሶ ነው ያሉት ዶክተር ዘሩባቤል፤ ‹‹በእውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ካፒታል ኢንቨስትመንት እና የውጭ ገበያን በሚመለከት



ዶክተር ዘሩባቤል ጌታቸው



ወይዘሮ አብረኸት መሃሪ



አቶ ሮባ ዳሜ

ሰፊ ሃላፊነት እንዳለብን እንረዳለን። በመሆኑም ዓለም ከደረሰበትና ኢትዮጵያ ከምትገኝበት ወቅታዊ ሁኔታም ሃላፊነታችንን አጠናክረን መቀጠል አለብን›› ሲሉም ነው የተናገሩት።

በብራሰልስ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ተመድበው የሚሰሩት ወይዘሮ አብረኸት መሃሪ፤ የተመለከቷቸው የቱሪስት መዳረሻ ስፍራዎቹ ከዚህ በፊት ብዙ ቱሪስቶችን ሲያስተናግዱ እንደነበር አስታውሰው፤ በቀጣይ የቱሪስት ፍሰቱ እንዲጨምር ከዲፕሎማቶች ጠንካራ ስራ መሰራት እንዳለበት መገንዘባቸውን ተናግረዋል።

በርካታ ኩባንያዎች እያመረቱ እንዳሉ ተመልከተናል፤ አሁን በአምራች ኢንዱስትሪው መቀዛቀዝ መኖሩን አይተናል፣ ተጨማሪ ኢንቨስተሮች ወደ አገር እንዲገቡ ማድረግ፣ የዲፕሎማቱ አንዱ ሃላፊነት እንደመሆኑ የንግድ አማራጮች እንዲገኙ በተሰማራንባቸው አገራት መስራት አለብን ነው ያሉት።

መንግሥት ለኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ የሰጠውን ትኩረት አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፤ ዲፕሎማቶች በተሰማራንበት አገር የሚገኙ ኢንቨስተሮችን ለማግባባትና አማራጭ የንግድ መዳረሻዎች እንዲኖሩ ለማድረግ ዝግጁ ነን ብለዋል። ባለድርሻዎችም ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ባለሀብቶችን በአግባቡ ተቀብለው የመጨረሻ ግቡን እንዲያሳኩ ክትትል ማድረግ እንደሚጠበቅም አሳስበዋል።

በኢትዮጵያ ኤምባሲዎች በአክራ እና በበርሊን መስራታቸውን ያስታውሱትና የመካከለኛው ምስራቅ ጉዳዮች ዳይሬክተር ሆነው የተመደቡት አቶ ሮባ ዳሜ በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች በአምራች ኢንዱስትሪዎችና በቱሪስት መዳረሻ ስፍራዎች ያደረጉት ጉብኝት የሥልጠናው አካል ነው ብለዋል።

በሥልጠናው ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድን ጨምሮ ከፍተኛ አመራሮችና የፖሊሲ አማካሪዎች ሥልጠና መስጠታቸውን፣ ከሥልጠናዎቹ በንድፈ ሃሳብ ያገኟቸውን ጉዳዮች በተጨባጭ በተግባር መመልከታቸውን አንስተዋል።

በለውጡ በተደረገው የኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብር መንግሥት በተጨባጭ እያከናወናቸው ያሉ ተግባራት ምን እንደሚመስሉ ከጉብኝቱ መገንዘባቸውንም ጠቁመዋል።

በተለይ በጦርነት ወቅት መንግሥት ኢኮኖሚውን ለማሻሻል፣ የዜጎችን ኑሮ ለመለወጥ እየሰራቸው የሚገኙ ስራዎች ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆኑ መረዳት ችለናል። አምራች ኢንዱስትሪዎች ከውጭ ገበያ ጋር በማስተሳሰር በዘርፉ የገበያ እድል እንዲፈጠር እንድንችል የሚያነሳሳን ነው ብለዋል።

ይህ ተግባር ለእኛ የዜግነትም የስራ ባህሪያችንም ነው። ኢንቨስተሮችን መመልመል፣ ወደ አገር እንዲገቡና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እንዲገናኙ ማድረግና በሂደቱ የሚፈጠሩ ችግሮች ካሉ እንዲፈቱ ችግሮቹን ማሳወቅ፣ ባለድርሻ አካላት በሃላፊነት ስሜት እንዲሰሩና የመንግስት ፖሊሲ በተፈለገው መልኩ እንዲተገበር የማድረግ ሃላፊነት አለብን። በከፍተኛ ተነሳሽነት እና ወኔ እንድንሰራ የሚያደርጉን ተጨባጭ ነገሮች መኖራቸውን በአካል ለመመልከት ችለናል።

# ብልጽግና ፓርቲ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ገለፁ።

“አቅምን በውጤት፤ ፈተናን በስኬት” በሚል መሪ ቃል ለብልፅግና ፓርቲ ከፍተኛ አመራሮች በሀዋሳ ከተማ የተሰጠው የሥልጠና መድረክ ማጠናቀቂያ ላይ የብልፅግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አደም ፋራህ እንደገለጹት፤ የብልፅግና ፓርቲን እቅዶች፣ ስትራቴጂዎችና ፖሊሲዎች በሙሉ ቁመና ለመተግበር አመራሩ የውስጠ ዴሞክራሲ ባህሉን ሊያሳድግ ይገባል። ይህን ተግባራዊ ማድረግም የተጠናከረ ፓርቲ እና የተጠናከረ መንግሥት መፍጠር ያስችላል።

በተለይም እንደ ሀገር የሚገጥሙንን ችግሮች በህብረ ብሔራዊ አንድነት የወንድማማችነት መንፈስ በጋራ የአንዳችን ቁስል የአንዳችን ህመም እንደሆነ ተረድተን ልንጋፈጣቸው እንደሚገባ ጠቅሰዋል።

ሌላው አቶ አደም ያነሱት ነጥብ አመራሩ እንደ ሀገር ለማከናወን ያቀድነው አካታች አገራዊ የምክክር መድረክ ስኬታማ እንዲሆን የበኩሉን እንዲወጣ የሚያስገነዝብ ነው።

በዚህም ሁሉም የብልፅግና ፓርቲ አመራር፣ መዋቅር እንዲሁም ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤቶች በከፍተኛ የሃላፊነት ስሜት የአገራዊ ምክክር መድረኩን ሃሳብ ሊያስፈፅሙ እንደሚገባ አሳስበዋል።

በሥልጠናው ላይ በርካታ የፓርቲው ከፍተኛ አመራሮች ተገኝተዋል። ፓርቲው የጀመራቸው የሰላም፣ የዴሞክራሲና የልማት መንገዶችን አጠናክሮ ማስቀጠል የሚችል አቅም በአመራሩ ዘንድ የሚፈጥር ሥልጠና ነበር ተብሏል።

ይህ የሥልጠና መድረክ ምርጫ ቦርድ ያስቀመጠውን ትእዛዝ በማክበር የፓርቲያችን 1ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አድርገን በጨረስን ማግስት የተደረገ ሲሆን በከፍተኛ አመራሩ ዘንድ ውስጣዊ አንድነትን በከፍተኛ ሁኔታ የሚያጠናክር እንደሆነ ከፓርቲው ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

# ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የተሰኙ የሽልማቱን አዘጋጅ ተቋማት ወደ አፍሪካ የወንድማማችነት እጆቻቸውን በመዘርጋታቸው እና የአፍሪካ ስኬታማ ሌጋሲ የሆነውን የኢትዮጵያ አረንጓዴ አሻራ ዕውቅና በመስጠታቸው አመስግነዋል፡፡

ዓለም በአየር ንብረት ለውጥ በእጅጉ እየተፈተነች ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ ኢትዮጵያ መፍትሄው ላይ አተኩራ እየሠራች መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በአራት ዓመቱ የአረንጓዴ አሻራ ንቅናቄ ከመላው የሀገሪቱ ክፍል 25 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ተሳትፈው 25 ቢሊዮን ችግኞች መተከላቸውንም አክለው አትተዋል፡፡

የኢትዮጵያ አረንጓዴ ሌጋሲ ኢኒሼቲቭ ከአማዞን ቀጥሎ በጣም ሰፊው የደን ልማትና የደን መልሶ ማልማት ፕሮግራም መሆኑን በመጥቀስም፤ ኢትዮጵያ ከችግኝ ተከላና ደን መልሶ ማልማት ሥራ በተጨማሪ ከ700 ሺህ ሄክታር በላይ የሚሆኑ የብዝሀ ሕይወት ሀብትና በካርቦን የበለፀጉ የተፈጥሮ ደኖችን በዘላቂና አሳታፊ የደን አስተዳደር መርሀ ግብር እያለማች መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የአረንጓዴ አሻራ ሌጋሲ ተነሳሽነት በተያዘው 2022 እየጎለበተ መምጣቱን ገልፀው፤ ሀገራዊ አረንጓዴ ባህል ማድረግ መቻሉንና የችግኝ ጣቢያዎች ቁጥር ከ121 ሺህ በላይ መድረሱን እንዲሁም ከ750 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ሴቶችና ወጣቶች የስራ እድል በመፍጠር 1 ነጥብ 3 ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር ገቢ እያስገኘ መሆኑን ጠቁመዋል።

ችግኞችን ወደ ጎረቤት አገራት በማሰራጨትም የቀጣናዊ ትስስር እና የድንበር ተሻጋሪ የሥነ ምህዳር አስተዳደርን ለማጠናከር እየተሠራ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

እንደ ሀገር ያለፈውን የምናይበት መነፅር እና የመጪውን የምንስልበት መንገድ ሊለያይ ይችላል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በልጆቻችን ባለን ተስፋ እና በፕላኔታችን ላይ ግን ሁላችንም አንድ ነን ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ በ2011 ዓ.ም የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብርን ስታስጀምር፣ በአራት ዓመታት ውስጥ 20 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ማቀዷ የሚታወስ ነው። ሆኖም በተጠቀሱት ዓመታት በመላ አገሪቱ 25 ቢሊዮን ችግኞች በመትከል የአራት ዓመት እቅዷን አሳክታለች። በዚህም የአየር ንብረት ለውጥን ለመቅረፍ እና ለደን መልሶ ልማት ላደረገችው አስተዋጽዖ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና አግኝታለች ሲል የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ዘግቧል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በትናንትናው ዕለት በተጀመረው የአፍሪካ -አሜሪካ የጋራ የመሪዎች ጉባኤ ላይ ለመሳተፍ ከትናንት በስቲያ ዋሽንግተን ዲሲ መግባታቸው ይታወሳል።

# “ኢትዮጵያን ከአጎዋ ተጠቃሚነት ማገድ የሰብአዊ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ጥሰት ምርመራ እንዲያደርጉ ከፈቀደ ብቻ ነው ማለቷን አምባሳደር ጥሩነህ ተችተዋል። በኢኮኖሚ ማዕቀቡ ኢትዮጵያ ወደ አጎዋ ተጠቃሚነት ካልተመለሰች ድሃው የማህበረሰብ ክፍል እንደሚጎዳና ይህም የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንደሆነ አመላክተዋል። ኢትዮጵያ የወሰደችውን እርምጃ በግልጽ ደጋግሞ በማስረዳት አቋማቸውን እንዲለውጡ ማግባባት እንደሚያስፈልግም አንስተዋል።

ገለልተኛ ቡድን ካልገባ ማለታቸው፤ “እኔ አቅም አለኝ፤ እኔ ያልኩትን መፈጸም አለባችሁ” ከሚል አቋም የመነጨ ነው ያሉት አምባሳደር ጥሩነህ፤ አቅም ያላቸው አገራት ሰብዓዊ መብትን ለፖለቲካ መሳሪያነት እየተጠቀሙበት እንዳለ፤ ይህም ምክንያት ማቅረቢያ መንገዳቸው እንደሆነና ለመጉዳት የሚፈልጉት አገር ላይ የሚፈጽሙት ተግባር እንደሆነ ጠቅሰዋል። ይህ አካሄድ ፍጹም ትክክል አይደለም ሲሉ ኮንነዋል።

እንደ አምባሳደር ጥሩነህ ገለጻ፤ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ገለለተኛ ከሆነው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ጋር ሆኖ የምርመራ ሪፖርት በማቅረቡ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚደረግ ድግግሞሽ መሠረተ ቢስ ነው። ይህንን በአገሪቱ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ጭምር የማስረዳትና በዲፕሎማሲያዊ መንገድ መታገል ይገባል።

“አቅም ያላቸው እርዳታ ሰጪ አገራት የራሳቸውን ፍላጎትና ፍረጃ ማንጸባረቅ እንጂ አገናዛቢ (ራሽናል) አይደሉም። ይህ የኖረ ነገር ነው። “ራሽናል” ባልሆን ዓለም ላይ እንዴት አድርጌ ጥቅሜን አስጠብቃለሁ ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል። ተግባራቸው ፍጹም ስህተት እንደሆነና ማን አለብኝነት የሚንጸባረቅበት እንደሆነ እያወቅንና እያየንም ቢሆን ለሕዝባችን ስንል አስፈላጊውን ነገር ማድረግ፤ እስከመጨረሻ ድረስ በምክንያታዊነት ለማስረዳት መሞከር ይኖርብናል” ሲሉ ገልጸዋል።

ኢ- ምክንያታዊ ጉዳዮችን ደጋግሞ ማንሳቱ በሠላም ስምምነቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊኖረው እንደሚችል የገለጹት አምባሳደሩ፤ የሠላም ስምምነቱን ለማድረግ ብዙ ርቀት እንደተኬደና ዓለምም በበጎ ሁኔታ እንደተቀበለው በመጠቆም፤ በዚህ ሁኔታ ላይ “ወደ ኋላ አናፈገፍግም” ብለዋል።

በዚህ ጉዳይ እንደ አሜሪካ ያሉ ሃያላን አገራት ጭምር ትልቅ ሥራ ቢሰሩም፤ ስምምነቱ የጎረበጣቸው “ኢትዮጵያ ለምን ለዚህ ችግሯ መፍትሄ አገኘች፤ አገሪቷን እንዲሁ መልቀቅ የለብንም፤ አንገቷን ይዘን እንድታጎበድድ ማድረግ አለብን የሚሉ” አንዳንድ አካላት የተጽዕኖ አራማጆች ሊኖሩ እንደሚችሉ አመላክተዋል። እነዚህ አካላት የአጎዋን አይነት ኢ-ምክንያታዊ ተጽዕኖ ትተው በኢትዮጵያ ሠላም እንዲሰፍን፤ ለልማትና ለሠላም ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር መርዳት እንዳለባቸው መክረዋል።

ችግሮችን ለመግታት በጋራ መሥራት ያስፈልጋል በማለት፤ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በሰብዓዊ መብት ኮሚሽን በሚደረጉ ውይይቶች፣ አፍሪካ አገራት አንድ ላይ ተሰብስበው በሚወስዱት እርምጃ መከላከል እንደሚገባ አስገንዝበዋል። አሁናዊውን የአፍሪካን ጥንካሬ ለዓለም አቀፍ መድረኮች ተጽዕኖ መፍጠሪያነት መጠቀም ይገባል ሲሉም ነው የተናገሩት።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በሙሰኞች ሴራ ወደኋላ የሚመለስ የጸረ ሙስና ትግል የለም!

ግጭት፤ ሁከትና ብጥብጥ የሕዝብን ሰላም ይነሳሉ። የአገርን ሀብት ያወድማሉ፤ ዕድገትና ብልጽግናን ይጎትታሉ፤ ድህነትንና ጉስቁልናን ያስፋፋሉ። በመጨረሻም ርሃብ፤ ስደትና መታረዝን በማስከተል ለአገር መፍረስ መንስኤ ይሆናሉ።

ግጭት፤ ሁከትና ብጥብጥ ባሉበት ሁሉ የመጀመሪያ ተጎጂዎቹ ንጹሐን ናቸው። በግጭት፤ ሁከትና ብጥብጥ ውስጥ ሰፊው ሕዝብ ለመከራ ይዳረጋል። ሕይወቱ አደጋ ላይ ይወድቃል፤ በሰላም ወጥቶ መግባት ብርቅ ይሆናል፤ ሰርቶ መለወጥ፤ ተምሮ ለቁም ነገር መብቃትና ነግዶ ማትረፍ እንደሰማይ ይርቃሉ። በምትኩም ድህነት፤ ጉስቁልና፤ ርሃብና ስደት የሕዝብ መገለጫዎች ይሆናሉ።

በተቃራኒው ግን ከግጭት፤ ሁከትና ብጥብጥ የሚያተርፉ አሉ። ሕዝብ ሲራብ የሚጠግቡ፤ ሕዝብ ሲፈናቀል ተደላድለው የሚኖሩ፤ ሕዝብ ሲከስር የሚያተርፉ፤ ሕዝብ ሲሰደድ በህንጻ ላይ ህንጻ የሚቆልሉ፤ ሕዝብ ሲሞት ሕይወት የሚዘሩ ጉደኞች በየስርቻው አሉ። ከእነዚህ ውስጥ ዋነኞቹ ደግሞ ሙሰኞች ናቸው።

ሙስኞች ከብርሃን ይልቅ ጨለማ ይመቻቸዋል። ከሰላም ይልቅ ጦርነት፤ ከመረጋጋት ይልቅ ሁከት፤ ከጸጥታ ይልቅ ብጥብጥ ምርጫቸው ነው። በጨለማ ውስጥ ነፍስ ይዘራሉ፤ በጦርነት ውስጥ ያተርፋሉ፤ በብጥብጥ ውስጥ ሀብት ያከማቻሉ፤ በሁከት ውስጥ ይዘርፋሉ፤ ሀብት ያሸሻሉ። ስለዚህም ጭር ሲልና ብርሃንን አይወዱም።

ኢትዮጵያ በሙስና ላይ አብዮት አውጃለች። ሙሰኞችንም ከያሉበት የማደን ሥራም የደኅንነት ተቋማትን ጭምር በዳሰሰ መልኩ ተጀምሯል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተገኝተው እንደተናገሩት ‹‹ቀዩን መስመር ቀይ ምንጣፍ›› ያደረጉ ሙሰኞች የአገር ስጋት ሆነዋል ሲሉ የችግሩን ክብደት አመላክተዋል። ሙሰኞቹም የመጨረሻ ጽዋቸውን ከመጨለጣቸው በፊት የያዙትን ሰይፍ በሕዝብ ላይ መምዘዝ ጀምረዋል። በቀበሩት ፈንጂም ሕዝብን በጅምላ ለማጥፋት የጥፋት ተልዕኮን አንግበው መንቀሳቀስ ጀምረዋል። በማንነትና በብሔር ሽፋን ድብቅ ዓላማቸውን ለማሳካት ብዙ ድንጋዮችን መፈንቀል ጀምረዋል። ለዚህ ደግሞ ሰሞኑን በአዲስ አበባና በወለጋ የተፈጠሩት ሁከቶችና ብጥብጦች ማሳያዎች ናቸው።

የብሔር ብሔረሰቦች አምባ የሆነችው አዲስ አበባ በርካታ ሴራዎች ተጠንስሰውላት፤ በርካታ እልቂት ታውጆላት ስትናጥ ከርማለች። ሙሰኞች ከመጋረጃው ጀርባ ተደብቀው ንጹሐን ተማሪዎችን በማያውቁት ፖለቲካ በማወናበድና የተለያዩ አጀንዳዎችን በማራመድ የሙስና ዕድሜያቸውን ለማራዘም በብዙ ታትረው ሲሰሩ ከርመዋል። ለእነሱ የማይጠረቃ ፍላጎት ንጹሐን ተማሪዎችን ጭዳ ለማድረግም በርካታ ርቀት ተጉዘዋል። ሆኖም ከሕዝብ ዓይንና ጆሮ የተሰወረ ነገር የለምና ምኞታቸው እንደጉም የሚያበንን የሕዝብ መድረክ ተካሂዶ ዓላማቸውን ማክሸፍ ተችሏል።

በተለይም የአዲስ አበባ አስተዳደር ባለፉት ቅዳሜና እሁድ ከተማሪ ወላጆች ጋር ባደረገው ውይይት የሙሰኞችና የሁከት ጠማቂዎች ሴራ አደባባይ ወጥቶ ተሰጥቷል። የድርጊቱ ፈጻሚዎች ራቁታቸውን ቀርተዋል። መንግስትና ሕዝብም እየተመካሩ በመስራት ከጀመሩት የጸረ ሙስና ትግል ለአፍታም ወደኋላ እንደማይሉ ግልጽ የሆነ መልዕክት አስተላልፈውላቸዋል።

ሰሞኑን ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ይፋ ባደረገው መረጃም ሙስና በኢትዮጵያ እየተከሰቱ ላሉ ግጭቶችና የሰላም እጦቶች ዋነኛ መንስኤ ነው። ሙስና ባለበት ግጭት፤ ብጥብጥና ሁከት የሰርክ ክስተቶች ናቸው። በኢትዮጵያም እየሆነ ያለው ይህ ነው። በተለይም መንግስት በሙሰኞች ላይ ግልጽ የሆነ ጦርነት ማወጁ እነዚህ የጥፋት ኃይሎች ከየተደበቁበት በመውጣት በዘረፉት ገንዘብ እዚህም እዚያም ሁከትና ብጥብጥ እንዲነገስና መንግስት ከያዘው አገርን የማበልጸግ ዓላማ ወደ ኋላ እንዲያፈገፍግ አልመው በመስራት ላይ ይገኛሉ። ሆኖም በሙሰኞች ሴራ ወደኋላ የሚመለስ ነገር እንደሌለ በግልጽ ተቀምጧል።

ለሙሰኞች ጊዜ መስጠት የተያዘውን የብልጽግና ጎዳና ወደ ኋላ ከመመለሱም በሻገር አገሪቱ በማያባራ ሁከትና ብጥብጥ ውስጥ እንድትኖር መፍቀድ ማለት ነው። ስለሆነም ከአፎቱ የተመዘዘው የጸረ ሙስና ካራ ሙሰኞችን ሳይቆርጥ ወደ ሰገባው መመለስ አይኖርበትም። የሙስና ዋና ተጠቂ የሆነውም ሰፊው ህዝብ ሙሰኞች የሚሰሩትን ደባ በመገንዘብ፤ በየስፍራው የሚፈጥሯቸውን ሁከትና ብጥብጦች በማውገዝና ብሎም ሙሰኞችን አሳልፎ በመስጠት የጸረ ሙስና ትግሉ ዋነኛ አጋር ሊሆን ይገባል። ዛሬ ኢትዮጵያ የምትፈልገው ከወሬ ይልቅ ተግባርን ብቻ ነውና!


**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73
ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# የአሸባሪው ሸኔ ነገር ...

**ዳንኤል ዘነበ**

በምስራቅ ወለጋ የተፈጠረውን ክስተት ስሰማ ከጥቂት ሳምንታት ገጥሞኝ የነበረን አሳዛኝ ክስተት አስታወሰኝ ። እለቱ እሁድ ነበር። ወደ አመሻሽ አካባቢ። ከአንድ የቅርብ ወዳጄ ጋር በመኖሪያ ቤቴ አካባቢ ሻይ ቡና እያልን ... የባጥ የቋጡን እናወጋለን።

በተለይ የሰሜኑን ጦርነት ለመቋጨት እየተደረገ ባለው ጥረት በእጅጉ መደሰቱን በስሜት ነገረኝ። እኔም በሃሳቡ እንደምስማማ በመግለጽ፤ የሰሜኑን ጉዳይ በሰላም ለመፍታት የሚደረገው ጥረት በልቤ ትልቅ ተስፋ እንደፈጠረ ነግሬው ‘በጉዳዩ ላይ ወደ ማብራሪያ ልሻገር ስል ፤ የወዳጄ የስልክ ጥሪ አቋረጠኝ ... ።

ተንቀሳቃሽ ስልኩን አንስቶ ሞቅ ባለ ድምጸት፤ Akkam jirtaa Hiriyaa Koo..(ጓደኛዬ እንዴት ነህ ...) አለ ፤ ከደዋዩ ሰው ምላሽ ተከተለ።

የወዳጄ ፊት በአንዴ ፍም መሰለ ፤ ዝግ ባለ ድምጸትም Malttu ummamee? (ምን ተፈጠረ?) ሲል ወዳጄ ጠየቀ.... ምላሹ ተከተለ ፤

በሰማው ነገር ግራ የተጋባው ወዳጄ፤ Fayeetu ajjifame?...enyuttu ajjesse? (ፈዬ ተገደለ?...... ማነው የገደለው?) ሲል ጠየቀ። (ፈዬ የዚህ ወዳጄ ታናሽ ወንድም ሲሆን፤ የህዝብ ትራንስፖርት ሹፌር ነው)፤ shaneitu ajjeesse (ሸኔ ነው የገደለው... ) የሚል ምላሽ ተሰማ ፤ እየተርበተበተ ...essattii ajjefame(የት ነው የተገደለው ...) ሲል በተስፋ መቁረጥ ሁኔታ ጠየቀ።

ስልኩን የደወለለት ሰው Nannoo magala maqiitti.....(መቂ ከተማ አካባቢ....) በማለት የታናሽ ወንድሙን ሞት እንደዋዛ አረዳው።

ጠዋት በስልክ አውርቶት በደስታ የተለየውን ታናሽ ወንድሙን ሞት የሰማው ይህ ወዳጄ ባለበት ደርቆ ቀረ ። ስለ ፖለቲካ ሳይሆን ስለ ሥራ ብሎ ከቤቱ የወጣው ወጣት በአሰቃቂ ሁኔታ ሕይወቱ ማለፍ ልብ ይሰብራል።

በእለቱ እንደ ፈዬ ሁሉ ስድስት በሚሆኑ ንጹሃን ላይ አሸባሪው፣ ጨፍጫፊው ሸኔ ሞት ፈርዶባቸዋል፤ በተከፈተባቸው የጥይት ሩምታ በርካቶች ቆስለዋል፣ ንብረት አውድሟል። ምስራቅ ወለጋ ላይ ንጹሃንን በተለይ የአማራ ተወላጆች ላይ ትኩረት ባደረገ መልኩ መግደል፣ መዝረፍ፣ ማፈናቀል የእለት ግብሩ የሆነው አሸባሪው ሸኔ በምስራቅ ሸዋ፣ በሰሜን ሸዋ መሰል ድርጊቶችን መፈጸም መጀመሩ ጉዳዩን ከባድ ያደርገዋል።

ይህ ሁኔታ ‘እቺ ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም’ የሚለውን ቆየት ያለ አባባልን ያስታውሰናል። ይህ ሁኔታ የአሸባሪው ቡድን እንቅስቃሴ ከጅምሩ በእንጭጩ መቋጨት አለመቻሉ የስጋትነቱ ደረጃ እየጨመረ እንዲመጣ ይጠቁመናል።

በአሁን ወቅትም ቡድኑ በኦሮሚያ ክልል በምሥራቅ ወለጋ፣ በምዕራብ ወለጋ ዞን፣ በምዕራብ ሸዋ፣ በምሥራቅ ሸዋ፤ በሰሜን ሸዋ ዞን አሸባሪው ቡድን የጥፋት በትሩን በሕዝቡ ላይ እያሳረፈ ይገኛል። የኦሮሚያን ክልል የሚያስተዳድረው መንግስት ሆነ የፌደራል መንግስት በኩል አሸባሪውን ቡድን ለማጥፋት ብዙ ስራዎች መሰራታቸው ይታወቃል። እየተሰሩም ይገኛል።

እዚህ ጋር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ኅዳር 6 ቀን 2015 ዓ.ም ከምክር ቤቱ አባላት ለተነሱ ጥያቄዎች የሰጡትን ማብራሪያ ማስታወስ ይገባል። “አሸባሪው ቡድን ትጥቁን ፈትቶና በሀይል የሚያደርገውን እንቅስቃሴ አቁሞ ወደ ሰላም ከመጣ መንግስት ለሰላም እና ለፖለቲካ ንግግር በሩ ክፍት ነው።

“ቡድኑ በኦሮሚያ ክልል ንጹሐንን እየገደለና እያፈናቀለ እንዲሁም የልማት ስራዎችን እያደናቀፈ ይገኛል። ከቡድኑ ጋር ያለው ችግር የሚፈታው ቡድኑ የኃይል እንቅስቃሴን አቁሞ ለፖለቲካዊ ንግግር ዝግጁ ሲሆን ብቻ ነው። ህግ የማስከበሩ ስራ በቀጣይም ተጠናክሮ ይቀጥላል” ነበር ያሉት።

ይህም በመንግስት በኩል ቁርጠኝነት እንዳለ አመላካች ነው። ነገር ግን የተሰሩት ስራዎች ምን ያህል ውጤት አምጥተዋል? የሚለው ምላሽ ይፈልጋል። በእኔ ግምገማ ግን ውጤቱ አርኪ ነው ለማለት የሚያስደፍር አይደለም። ይህን ለማለት ያስደፈረኝ ደግሞ ከሰሞኑ በምስራቅ ወለጋ አንገር ጉቴ የተፈጠረው ክስተት ነው።

በዚሁ አካባቢ የአሸባሪው ቡድን አጸያፊ የጭፍጨፋ ገድል ዳግም በንጹሐን ላይ ሲነበብ፤ ዜጎች በብሔራቸው እየተመረጡ ተገድለዋል። በእርግጥ መንግስት መከላከያ ሰራዊቱን ወደ ምስራቅ ወለጋ አንገርጉቲ ከተማ አቅንቶ ችግሩን ለመቆጣጠር ችሏል። ግጭቶች ሳይከሰቱ ምላሽ መስጠት፣ ግጭቶች ከተከሰቱ በኋላ ምላሽ ከመስጠት በብዙ እጥፍ ይሻላል።

ግጭቶች ከተከሰቱ በኋላ ምላሽ መስጠት ደግሞ ምላሽ ካለመስጠት እንደሚሻል አይካድም። ነገር ግን የማይካደው ሃቅ የ ሸኔ አላማ ቢስ እንቅስቃሴ አንድ ቦታ እንዲቆም አድርጎ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መፍትሄ ማበጀት ካልተቻለ ውሎ ሲያድር ችግሩ ውስብስብ የመሆኑን አይቀሬ ነው።

በዚህ ረገድ ደግሞ የፌደራል መንግስት ሆነ የክልሉ መንግስት ትልቅ የቤት ስራ ይኖርባቸዋል። በተለይ ደግሞ ክልሉን የሚያስተዳድረው መንግስት የኦሮሞ ህዝብም ሆነ በክልሉ የሚኖረው ሕዝብ አሸባሪው ሸኔ እያደረሰ የሚገኘውን መከራ፣ ግፍና ሞት ማስቆም ይኖርበታል።

ከሕዝብ ጋር ተቀናጅቶ ክልሉን ‘የኦሮሞን ሕዝብ አንገት እየቀሉ የኦሮሞን ሕዝብ ነጻ አወጣለሁ ከሚለው የአውሬዎች ስብስብ ነጻ ሊያደርግ ይገባዋል። የሕዝቡን ሰቆቃ ማስቀረት የሚያስችል እርምጃ በመውሰድ እንባውን ማበስ ያስፈልጋል።

ይህን ለማድረግ የክልሉ መንግስት ሙሉ አቅም ይኖረዋል ብዬ አምናለሁ። ራሱሙ በአደባባይ ማረጋገጫ ሰጥቷል። በሌላ በኩል ደግሞ የኦሮሚያ ክልል መንግስት አመራሩን ፣ የጸጥታ መዋቅሩን በሚገባ መመርመርና መፈተሽ አለበት።

የጠላትን ዓላማ ለማሳካት የሚጣጣሩ ግለሰቦችን በጉያው ይዞ የሚደርግ ዘመቻ ውጤቱ ያው ክስረት ፣ ክሽፈት ይሆናል። ስለዚህ ለጠላት መረጃና ካራ እያቀበሉ ሕዝብን የሚያስለቅሱትን ከሃዲዎችን ከውስጡ መመንጠር ይኖርበታል።

ራሱን አጽድቶ ከሕዝብ ጋር ወደተቀናጀ እርምጃ መሻገር ጊዜ ሊሰጠው የሚገባ አይደለም። ነገር ግን አሁን ባለው አካሄድ የሚቀጥል ከሆነ የአሸባሪው’ ሸኔ ነገር ‘እቺ ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም’ እንዳይሆን አገሩን እንደሚወድ አንድ ዜጋ እሰጋለሁ ።

## ፍረዱኝ

# ዓመታትን የዘለቀው የነዋሪዎች ቅሬታ

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ የኖሩ ነዋሪዎች ከተወለድንበት፣ ካደግንበት፣ እትብታችን ከተቀበረበትና ክፉ በጎን ካየንበት የሚያፈናቅለን አሰራር በመምጣቱ ስለነገው ስጋት ጥሎብናል፤ ለዛሬም በእጅጉ ተቸግረናል ሲሉ ነበር አዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ድረስ በመምጣት መንግስት በደላችንን ይስማ፤ ህዝብ ይፍረደን ለታሪክም ይቀመጥልን ሲሉ ቅሬታቸውን ያቀረቡት።

የዝግጅት ክፍላችን ቅሬታውን በመቀበል ጉዳዩ ምን ያህል እውነት ነው ሲል ግራ ቀኝ የሚመለከታቸውን አካላት በማነጋገር ‹‹ፍረዱኝ›› በሚለው አምዳችን አስቀምጠን፤ የሚመለከታቸው አካላት በሚጠበቅባቸው ልክ ኃላፊነታቸውንም እንዲወጡ ለማሳሰብና ህጋዊ አሰራሮች ይሰፍኑ ዘንድም ለመጠቆም ከመሻት የተነሳ ለንባብ አብቅተናል።

የአካባቢው ነዋሪዎች በብዛት የሚያቀርቧቸው ምክንያቶች በአንድም ይሁን በሌላ ተቀራራቢ ናቸው። ነገር ግን ተበድለናል የሚለው የበደላቸውን ጥግ ለመግለፅ የተለያዩ ቃላትን ተጠቅመው ይሆናል እንባቸውም የብሶታቸው መገለጫ ነው። ‹‹አቡ ጨፌ›› በሚባለው አካባቢ ለዘመናት ኖረናል የሚሉት ነዋሪዎቹ ለልማት ይፈለጋል በመባሉ ምክንያት የመተዳደሪያ መሬታችን እና በዓመት ሦስት ጊዜ ከምናመርትበት የጥሪት መሰረታችን ከሆነው ለም መሬት ተፈናቅለን የበይ ተመልካች ሆነናል ይላሉ።

‹‹የተወሰደው መሬት የምትታለብን ላም ከአንድ አርሶ አደር ቤት ከመውሰድ ቢገዝፍ እንጂ አይተናነስም ››ሲሉ የችግራቸውን ግዝፈት ለመግለፅ ይሞክራሉ። ከምን በላይ የሚያንገበግባቸው ደግሞ በወቅቱ ካሳ ተብሎ የተከፈላቸው በፍፁም ተቀባይነት የሌለውና ሁሉንም ነገር በጉልበት እንደነበር ያስታውሳሉ። በርካቶቹ አርሶ አደሮች በመሆናቸው በማስፈራራትና በግድ በማስፈረም የተከናወነ በመሆኑ፤ የሰብዓዊ መብታቸው ጥሰት እንደተፈፀመባቸው ይነገራሉ።

ለዓመታት ቅር ተሰኝተው ግማሹ ጥቂት ካሳ ወስዶ ከፊሉ ደግሞ ምንም ሳይወስድ በቁዘማ ውስጥ ዛሬም ድረስ በችግር ውስጥ መሆናቸውን ይነገራሉ። ለዚህም አስረጅ የሚሉትን በሙሉ ነዋሪዎች እንዲህ ያቀርባሉ።

በወረዳው የምክር ቤት አባል ነኝ ይላሉ ወይዘሮ አስካለ አያሌው። ይህ በደል ለዓመታት በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ከፍተኛ ቅሬታ የፈጠረ ስለመሆኑ ጠንቅቄ አውቃለሁ ይላሉ። ይህም ብቻ ሳይሆን እኔም በዚህ ሰበብ ከፍተኛ በደል እየደረሰብኝ ነው ባይ ናቸው። የአካባቢው ማህበረሰብ 10 ዓመት ሙሉ በደል ደርሶብናል፤ የመንግስት አካል ወረድ ብሎ ሊመለከተን ይገባል። እዚህ አካባቢ እንባ ጭምር ተመልካች አጥቷል ይላሉ።

እንደ ወይዘሮዋ ገለፃ፤ የአካባቢ ነዋሪዎች ቀደም ሲል በዓመት ከሦስት እስከ አራት ጊዜ ጎመን፣ ቲማቲም፣ ድንች፣ ቃሪያ እና የመሳሰሉትን እያለሙ ከእለት ጉርሳቸው ተርፎ ለነገ በማለት ይቆጥቡ እንደነበር ያስታውሳሉ። ከአቃቂ ቃሊቱ ፍራፍሬዎችን እና የጓሮ አትክልቶችን ወደ ፒያሳ አትክልት ተራ በመላክ ጠቀም ያለ ገንዘብ ከማግኘታቻው በተጨማሪ የተደላደለ ሕይወትም ይመሩ ነበር። ዳሩ ግን በልማት ስም ቦታውን እንዲለቁ ከተደረገ በኋላ እና ተመጣጣኝ ያልሆነ ካሳ እንዲወስዱ ከተወሰነባቸው በኋላ በርካቶች ለከፋ ድህነት ተጋልጠዋል፤ የመንግስት እጅ ጠባቂ ሆነዋል፤ ግማሹ ደግሞ ለሰው መትረፉ ቀርቶ የቀን ሠራተኛ ሆነዋል ሲሉ የአካባቢ ነዋሪዎች ይናገራሉ።

እኔም የወረዳው ምክር ቤት አባል እንደመሆኔ መጠን ጉዳዩን ደጋግሜ ሳነሳው ተቀባይነት አጥቻለሁ። ስለጉዳዩ ደጋግሜ ማንሳቴ ለሌላ ችግር ዳርጎኛል። በተለይም ደግሞ ነዋሪዎች መብታቸውን እንዲጠይቁ ትገፋፊያለሽ፤ የልማት ተቃዋሚ ነሽ በሚልና በሌላ ሰበብም በነገር ሸንቆጥ እንደሚያደርጓቸው ይጠቁማሉ። ይህም ብቻ ሳይሆን ይባስ ብሎ በገዛ ግቢያቸው ውስጥ ቤት ለመገንባት ፈቃድ ቢጠይቁም ተከልክለዋል። ሌላው ቀርቶ የመኖሪያ ቤታቸውን ለማደስ በአየር ካርታ እና መሬት ካርታ አይናበብም በሚሉ ተልካሻ ሰበቦች ምንም መስራት እንዳይችሉ መደረጋቸውን ይናገራሉ። ለግንባታ ብለው የገዙት አሸዋ እና ጠጠር በዓመታት ብዛት ጥቅም አልባ ሆኖ ሳር እንደበቀለበት በመጠቆም፤ አሁንም የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው ማሳሰብ እፈልጋለሁ፤ እንደ ምክር ቤት አባልነቴም በህጋዊ መንገድ መጠየቄን አላቆምም ብለዋል።


ፎቶ-ገበዞ ገብሬ

የአቡ ጨፌ አካባቢ ነዋሪዎች

**የ10 ዓመት ካሳ ተብሎ የተሰጠው እኛ በአንድ ዓመት ውስጥ የምናገኘው ሲሆን በአንድ ካሬ 37 ብር ታስቦ ነው የተሰጠን። ይህ ደግሞ በየትኛም ሳይንሳዊ መመዘኛ ተቀባይነት የሌለውና የወቅቱ አመራሮች በማስፈራራት የፈፀሙት ስለመሆኑ መረጃዎቹ በራሳችው ምስክሮች መሆናቸውን ይገልጻሉ**

### ከወቅቱ የኮሚቴ አባል እና ከነዋሪዎች አንደበት

ይህ ችግር ዓመትን ያስቆጠረ እና አሁንም ድረስ እልባት ያልተሰጠው ግን ደግሞ በየጊዜው ተደጋጋሚ ጥያቄ ያልተለየው መሆኑን የሚናገሩት ደግሞ በወቅቱ የካሳ ክፍያ ኮሚቴ አባል የነበሩት አቶ ደሳለኝ ንስሮ ናቸው። ችግሩ የተወሰኑ ግለሰቦች ብቻ አይደለም፤ እኛ ኮሚቴዎች ጭምር ፍዳ የበላንበት ነው ሲሉ ያሳለፉትን የድካም ጊዜ ያስታውሳሉ ።

በወቅቱ የኮሚቴ አባል ብንሆንም ብዙ ትግል ሳደርግ ነበር የሚሉት አቶ ደሳለኝ ይህ ሁሉ ፈተና ደርሶብን አንዳችም ጠብ ያለነገር ሳናገኝ ይኸው ከዛሬ ደርሰናል ይላሉ። አሁንም ቢሆን ተስፋ አንቆርጥም ይልቁንም ህጋዊ መብታችን ለማስበር በተቻለ መጠን የአቅማችንን ሁሉ ተጠቅመን በህጋዊ መስመር ለመጠቀም ጥረት እናደርጋለን ብለዋል።

በወቅቱ ኮሚቴ ሆነን ይህ የካሳ ግምት ፈጽሞ አግባብ አይደለም ብለን ተቃውመናል። የአካባቢ ማህበረሰብ ልማት ቢፈልግም ከኑሮ መሰረቱ የሚያናጋውን ልማት ግን አንፈቅድም ብለን ተከራክረናል። እነርሱ ግን እኛን ለማሞኘት ብዙ ነገር ብለውናል። በሰፈራችሁ ትምህርት ቤት ይገነባላችኋል፤ ውሃና መብራት ይቀርብላችኋል፤ ጤና ጣቢያና ሌሎች መሠረተ ልማቶችም ይሟሉላችኋል ብለው ሊያረጋጉን ሞከሩ፤ ቃልም ገቡ ይላሉ። ቃል ከገቡት ውስጥ ግን የመስመር ውሃ አግኝተናል፤ ከዚያ ውጭ ሌላው የተገባልን ቃል የውሃ ሽታ ሆኗል።

እኛም በወቅቱ አንፈርምም ወይንም ደግሞ ይህ አግባብ አይደለም ስንላቸው የበላይ አመራሮች የነበሩት በከፍተኛ ደረጃ እያስፈራሩን፤ ግዴታ ያለመንበትን ነገር አድርጉ ብለውን ከህዝቡም ከራሳችን አጣልተውናል፤ አመኔታም እንድናጣ አድርገውናል ይላሉ። በአሁኑ ወቅት ደግሞ ህዝቡን የሚሰማ መንግስት በመኖሩ መፍትሄ ሊሰጠን ይገባል።

አቶ ፀጋዬ ሽኩሬ ፍትህን ፍለጋ ከ10 ዓመት በላይ መንገላታታቸውን ይገልፃሉ። እስከዛሬዋ ቀን ድረስ ይህን ጉዳይ አታንሳ በሚል ከአንዳንድ ኃላፊዎች ማስፈራሪያ እና ዛቻ እየደረሰባቸው ስለመሆኑ ይናገራሉ። የመንግስት ልማትን ደግፈን ታዛዥ መሆናችን ችግር ይዞብን መጥቷል ባይ ናቸው። በወቅቱ የተባልነው ለአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን መስመር የሚዘረጋበት አካባቢ በመሆኑ የተወሰነ የእርሻ ቦታ ልቀቁ ብለውን በወቅቱ በደስታ ለቀናል።

መንግስት የሚሰራው ልማት በእጅጉ እንደግፋለን፤ በቀጣይም ልማት እንሻለን የሚሉት አቶ ጸጋዬ በርካቶችን እያፈናቀሉ ጥቂቶችን ብቻ ለማበልጸግ የሚፈፀም ስውር ወንጀል መቆም አለበት መንግስትም ችግራችንን ሊሰማ ይገባል ሲሉ ይናገራሉ። የ10 ዓመት ካሳ ተብሎ የተሰጠው እኛ በአንድ ዓመት ውስጥ የምናገኘው ሲሆን በአንድ ካሬ 37 ብር ታስቦ ነው የተሰጠኝ። ይህ ደግሞ በየትኛም ሳይንሳዊ መመዘኛ ተቀባይነት የሌለውና የወቅቱ አመራሮች በማስፈራራት የፈፀሙት ስለመሆኑ መረጃዎቹ በራሳቸው ምስክሮች መሆናቸውን ይገልጻሉ። መሬታችሁ 10 ዓመት የሚሰጠውን ምርት አስበን ካሳ ከፍለናል ብለው ቢያስፈርሙንም የተሰጠን ካሳ ግን የአንድ ዓመት ብቻ ነበር ይላሉ። በዚህ ውስጥ ደግሞ እኔን ጨምሮ ካሳ ለወሰድነው፤ የዕጽዋት ግምት ያልተገመተልን አለን፤ እስካሁንም ከበደል ጋር እየኖርን ነው ብለዋል።

ተክሉ ንስሮ እና ኢንስፔክተር አብረሃም ፉጂ ለዓመታት የበደሉን ቀንበር ተሸክመን ይኸው ዛሬ ደርሰናል ሲሉ የምክር ቤቱን እና የወቅቱ የኮሚቴ አባላትን ሐሳብ ይጋራሉ። ዳሩ ግን ዛሬም ድረስ ችግሩ እንደ ችግር ከመወራት የዘለለ መፍትሄ አለመገኘቱ ግን ያንገበግባቸዋል።

‹‹የወተት ላም ተቀምተን ወተት እንዲያምረን፤ ኑሮ እንዲመረን ያደረገ ሥርዓት ነበር››፤ አሁንም የዚያ ሥርዓት ርዝራዦች በመኖራቸው በደላችንን እንኳን በመናገራችን እየመጡ ያስፈራሩናል። ይህን ጉዳይ ወደፈለጋችሁበት ብትወስዱትም የተለየ ነገር አታመጡም አርፋችሁ ኑሯችሁን ብትመሩ ይሻላችኋል እያሉ እንደሚያስፈራሯቸው ነው የሚናገሩት።

ኢንስፔክተር አብርሃም በወቅቱ በፖሊስ ሙያ ውስጥ ያገለግሉ እንደነበርና ጉዳዩን ሲከታተሉ እንደነበር ያስታውሳሉ። ዳሩ ግን በአጭር ጊዜ እልባት ይሰጠዋል የተባለው ጉዳይ ያለአንዳች መፍትሄ ዓመታትን ማስቆጠሩ እንዳሳዘናቸው ይጠቁማሉ።

በተለይም እንዳንዱ ድርጊት በምን ህግና ደንብ እየተከወነ ነው ብሎ ለሚጠይቃቸው መንግስት የወሰነው ነው ከማለት ውጭ የተለየ ህጋዊ አሰራር መከተል ያልፈለጉ አመራሮች እንደነበሩ ያስታውሳሉ። ዳሩ ግን ችግሩ እየተንከባለለ መጥቶ አሁንም መፍትሄ አለማግኘቱ ደግሞ የበለጠ አግራሞት እንደፈጠረባቸው ያስረዳሉ።

**ሴሳው ችግር**

ይህም የካሳ ጉዳይ አልበቃ ብሎ እንደገና አካባቢውን የሚቀራመቱ ባለሃብቶች መንደሩን መከበባቸውንና የአካባቢውን ነዋሪዎች ያላማከለ እና በልማት ያላቀፈ ነውር እየፈፀሙ ተመልካች አጥተናል ይላሉ። አካባቢው ለትልልቅ ግንባታዎች የሚውል ልዩ ድንጋይ በአካባቢው አጠራር ‹ካባ› የታደለ ቢሆንም ነዋሪዎች ከበረከቱ ከመቃመስ ተከልክለው ከመንግስት ጋር ሆድና ጀርባ እየሆኑ መጥተዋል።

ጥቂት ግለሰቦች ከመንግስት ፈቃድ አለን በሚል ሰበብ ብቻ አካባቢውን እየቆፈሩ በጉልበት እየወሰዱብን ነው። ሌላው ቀርቶ እኛ ያደግንበት፣ የተወለድንበት እትብታችን የተቀበረበት እንስሳቶቻችን ይወሉበት የነበረ የጋራ ሃብታችንና ንብረታችን ነው ብለን ለሚመለከተው ሁሉ አቤት ብንልም ሰሚ አጥተናል። ይህ ሁሉ ሆኖም ካሳ ይከፈለን ስንል ይከፈላችኋል ከመባል የዘለለ በተግባር ጠብ የሚል ነገር አለመኖሩ አሳዛኝና ህዝብና መንግስት ሆድና ጀርባ ያደረገ ልማት ነው በማለት ይኮንናሉ።

ቀደም ሲል የአካባቢው ነዋሪዎች ተደራጅተው ካባው አውጥተው ይሸጡ እንደነበርና በዚያው መንገድ ተደራጅተው አሁን መስራት እንደሚችሉ ይጠቁማሉ። ነዋሪዎች ግን ከምንም በላይ አንድ ነገር ይጠይቃሉ። አንድ ግለሰብ ወይንም ድርጅት ባለሃብት በሚል ካባ ፈቃድ ሲሰጠው መስፈርቶቹ ምንድን ናቸው ሲሉ ይጠይቃሉ። ባለሃብት የቴክኖሎጂ ግብዓትና ሽግግር ካልጨመረ እና መሬት ውስጥ ብቻ ያለውን ድንጋይ ቆፍሮ ማውጣት ከሆነ ከእኛ ከአርሶ አደሮች የተለየ ብቃትና ብልሃቱ ከምን ላይ ነው ሲሉ ይጠይቃሉ። የአካባቢው ነዋሪዎች ጋር ግብግብ በመግጠም ጥዋትና ማታ ፖሊስ እያቆመ ድንጋይ የሚያሸሹ ግለሰቦች እንዴት ባለሃብት ተብለው ሊጠሩ ይችላሉ፤ ከህዝብ ተጣልተው ለማንስ ይሠራሉ፤ ይህ ኢንቨስትመንት ሳይሆን በጠራራ ፀሐይ አርሶ አደሮችን መበዝበዝ ነው ሲሉ ምሬታቸውን ይገልፃሉ። አስገራሚ የሚሆነው ደግሞ ካባ ድንጋይን ሲያወጡ አካባቢው ላይ ያለውን አትክልት ከማበላሸትም በተጨማሪም በስፍራው ትልቅ ጉድጓዶችን ትተው ለህዝብ ሌላ መከራ እየጨመሩ መሆናቸውንም ያብራራሉ።

**በወቅቱ የነበሩ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል**

በወቅቱ አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ድረስ በመሄድ ካሳ እና አርሶ አደሮችን ቅሬታ አስመልክቶ ህዝቡን ማወያየታቸውን የሚያስታውሱትና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የነበሩት ዶክተር ተመስገን ቡርቃ፤ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ስር ያሉ በርካታ አርሶ አደሮች ቅሬታ ማቅረባቸውንና መፍትሄ እንዲሰጣቸው አቅጣጫ መቀመጡን ይጠቁማሉ። በወቅቱ በአብዛኛው ይነሳ የነበረው ችግር የካሳ ግምቱ በጣም ዝቅተኛ ስለሆነ ፍትሃዊ አሰራር ይንገስ በሚል የቀረበ መሆኑን በማስታወስ መጨረሻ ላይ ግን ለልማት ሲባል የተፈናቀሉ አርሶ አደሮችን በተመለከተ በመንግስት ይሁንታ ጽህፈት ቤት እስከማቋቋም የደረሰ ነው። በመሆኑም የአርሶ አደሮቹ ችግር በዚህ አግባብ እንደሚፈታ እገምታለሁ ባይ ናቸው።

**ምላሽ - የክፍለከተማው ዋናስራ አስፈፃሚ**

ዶክተር አበራ ብሩ የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ዋና አስፈፃሚ ናቸው። የመልካም አስተዳደር ችግር በክፍለ ከተማው በስፋት መኖሩን የሚናገሩት ዶክተር አበራ፤ በክፍለ ከተማው አቡጨፌ አና መሐመድ ካፌ የሚባሉ ካባ የሚወጣባቸው ስፍራዎች መኖራቸውንና ነባር መሆናውንም ይገልጻሉ።

እዚህ ላይ ሁለቱም በራሳቸው ነባር ካባ (የድንጋይ መፍጨ) ናቸው። ይሁኑ እንጂ በዚህ አካባቢ የሚነሱ ጥያዎች መልክ ብዙ ናቸው። አንደኛው ማህበረሰቡ እኛ ራሳችን ካባውን አውጥተን ለመንግስትም አካል ይሁን ለሚፈለገው አገልግሎት ማዋል እንችላለን የሚል ነው። ሌላኛው ቅሬታ ደግሞ ካባውን ለማውጣት በሚደረግ ጥረት ፈንጂዎች መሬት ውስጥ ስለሚቀበሩ የአካባቢው ነዋሪዎች በከፍተኛ ድምፅ እየረበሸ እና በህፃናትን ላይ ጭምር ከፍተኛ ድንጋጤ እያሳደረ ነው የሚል ተደጋጋሚ ቅሬታ ነበር። አካባቢውን እያወከና ለጤናችንም ትልቅ እክል እየፈጠረ ነው። ፍንዳታው የቤት እቃ እስከመስበር ደርሷል የሚል ነው።

ካባው በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለከተማ ከሚገኙ 13 ወረዳዎች መካከል በስምንቱ ውስጥ ይገኛል። ነገር ግን የወረዳ ስምንት ነዋሪዎች ለየት የሚያደርገው የራሱ የሆነ ምክንያት ሊኖር ይችላል። ነዋሪዎቹ ካሳ አልተከፈለንም በሚል በተደጋጋሚ ላቀረቧቸው ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ጥረት ተደርጓል። በዚህም የተነሳ ለነዋሪዎቹ ካሳ እንደሚከፈል የማስተማመኛ ወረቀት ተሰጥቷቸዋል። ካሳ የሚጸድቀውም በከተማ አስተዳደሩ ሲሆን የክፍለከተማው መሬት አስተዳደር በሥርዓት ልኬቱን ሰርቶ መላኩን ይናገራሉ። ከዚህ በዘለለ ግን በአካባቢ ካባ እያወጡ ያሉ አካላት በየትኛው መንገድና ሁኔታ ለማየት በተደረገው ጥረት ሁሉም ህጋዊ መሆናቸው ያረጋግጣሉ። በመሆኑም አርሶ አደሮቹ ለሚያቀርቡት ቅሬታ ካሳ ከተማ አስዳደሩ በሚወስነው መሰረት የሚከፈል ይሆናል ብለዋል።

ዳሩ ግን የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ለምን ይሆናል ሲል ይጠይቃል። ‹‹አርሶ አደሮቹ ግብር ሲከፍሉበት በነበረበት ቦታ እና በቀጣይም ጥሩ ገቢ እናገኝበታለን ብለው በሚያስቡት ቦታ ላይ ምንም ግብር ሳይከፈል ለአልሚ መሰጠቱ ከህግና ከሞራል አኳያ እንዴት ይታያል፤ ባለሃብቱ እየተጠቀመ አርሶ አደሮቹን ካሳ ይከፈላችኋል ጠብቁ ብሎ ማንገላታት ህጋዊ ነውን፤ ባለሃብቶቹ ለአካባቢው ማህበረሰብ አንዳች የሚፈይድ ነገር ሳይሰሩ ካባ ብቻ አውጥተው መሄድ በምን አግባብ ይታያል ሲል ይጠይቃል። በተጨማሪም ካሳው መቼ እንደሚከፈላቸው እርግጠኛ ባልሆኑ አርሶ አደሮችና ቤተሰቦቻቸው ላይ ለሚፈጠር ሥነ-ልቦናዊ ጫና ማንስ ይጠየቃል ሲል ነበር ጥያቄውን ያቀረበው?


የትኛው የካሳ አሰራር በመንግስት ህጋዊ አሰራር የሚመራ ሲሆን ከፋዩም መንግስት ራሱ ነው የሚሉት ዶክተር አበራ፤ ነገር ግን በቦታው የሚያለማው ባለሃብት ከመንግስት የሚጠበቅትን ግዴታ መወጣት አለበት። ይህን በማድረግ በኩል ባለሃብቶቹ ህጋዊ አግባብ ተከትለው እየሰሩ ስለመሆኑ ያገኘነው መረጃ ያረጋግጣል። አሰራሩ ይህ ከመሆኑም በተጨማሪ እኛ በአሁኑ ወቅት የሰጠው ካባ የለም፤ በአሁኑ ወቅት እያወጡ ያሉት ቀደም ሲል የወሰዱት ፈቃድ ስለሆነ ይህን ስራ አቁሙ ማለት አይቻልም። ይሁንና በአሁኑ ወቅት ካባ የማውጣት ፈቃድ የሚሰጠው ከማዕከል ነው ይላሉ። በመሆኑም ግብዓቱ ያለበትን ቦታ መረጃ ከመስጠት የዘለለ ሥራ አንሰራም። ከዚህ በተረፈ ግን ነዋሪዎችም የሚሉት ካሳው ዘገየ ነው፤ ይህ ጥያቄያቸው ግን ህጋዊና አግባብ ነው ከተማ አስተዳደሩ በተላከለት መረጃ መሰረት ወደታች ሲያወርደው በቅጽበት የሚከፈላቸው ይሆናል። ከዚህ በዘለለ ግን አልሚዎቹ ካባውን እያወጡ ያሉት መንግስት ለሚያከናውናቸው የመንገድ መሰረተ ልማትና ለመሳሰሉት ስለሆነ ሥራውን አቁሙ ማለት ችግሩን የባሰ ውስብስብ ማድረግና ልማቱን ማደናቀፍ እንደሆነም ያብራራሉ።

ዶክተር አበራ እንደሚሉት አቡ ጨፌ አካባቢ ያሉ ነዋሪዎችም ከካሳ ክፍያ ጋር በተያያዘ የሚያቀርቧቸው ጥያቄዎችም በራሱ ማዕቀፍ የሚታይ መሆኑን ያብራራሉ። በወቅቱ ካሳ የተከፈላቸው ቢሆንም በቂ አለመሆኑን መረዳት ተችሏል። 10 ዓመት ሙሉ በካሳ ጉዳይ ጥያቄ እያቀረቡ ስለመሆኑ በቂ መረጃ የለኝም፤ ነገር ግን ጥያቄያቸው ካሳ ይከፈለን ሳይሆን የካሳ ልዩነት ይከፈለን የሚል ነው። ይህም በወቅቱ የተሰጠው የካሳ ግምትና በአሁኑ ወቅት ያለው ግምት እንደማይገናኝ መረዳት ችለናል ይላሉ። ካሳ ልዩነቱም እንደሚከፈል ከግምት ውስጥ ማስገባት የተቻለ ሲሆን፤ ለዚህም የማስተማመኛ ደብዳቤ የተሰጠ መሆኑን እናውቃለን።

እንደ ዶክተሩ ማብራሪያ፤ አርሶ አደሩ ዕትብቱ የተቀበረበትን ሰፈር እስከ መጨረሻው ሲለቅና ሲፈናቀል ሲሰጠው የነበረው ካሳ መልሶ የሚያቋቁማቸው አይደለም። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት አካሄድም ፍትሃዊነት የጎደለው እንደነበር ከሁኔታዎች መረዳት እንደሚቻልና ይህ ምንም አጠያያቂ እንዳልሆነ ይጠቁማሉ።

በነበሩ ፕሮጀክቶች ላይ ይዞታቸው ለሌላ አልሚ ወይንም የመሬት ባንክ የገባ መሬት መሆኑ ይታወቃል። ይሁንና ካሳ ልዩነት የሚከፈላቸው በወቅቱ ከነበረውና በአሁኑ ወቅት ካለው ግምት ጋር በማነፃፀር ነው። በወቅቱ አንድ ካሬ ከ60 ብር በማይበልጥ ግምት የተሰጣቸው ሲሆን ይህ ግን በአሁኑ ወቅት ማስተካከያ ተደርጎ የግጦሽ ወይንም እርሻ ሲሆን በካሬ ተሰልቶ 1800 ብር ይከፈላል። በመሆኑም በዚህ መሃል ለው ልዩነት ሲታይ እንደተከፈለ አይቆጠርም። ‹‹አንዳንድ ቦታ እየተጠየቀ ያለው ግን የካሳ ክፍያ ብቻ ሳይሆን የቀድሞ መሬታችንን መልሱልን የሚል ነው። አንድ ግን መታወቅ ያለበት ጉዳይ በሦስተኛ አካል ወይንም እጅ የገባ መሬት ወደ አርሶ አደር የመመለስ ዕድል የለም›› ብለዋል።

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ በርካታ መልካም አስተዳደር ጥያቀዎች መኖራቸውን ይጠቁማሉ። ለአብነትም የኢንዱስትሪ መንደር በቂሊንጦ ሲቋቋም ከነጭራሹ ካሳ ያልተከፈላቸው አርሶ አደሮች አሉ። የኢትዮጵያ ምግብና መድሃኒት ቁጥጥር በአቃቂ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 የገነባው ግንባታ ላይ አንዳች ካሳ አልከፈለም፤ ይሁንና በርካታ አርሶ አደሮች ተፈናቅለዋል። ከዚህም በተጨማሪ ከካሳ ጋር በተያያዘ ጥያቄ የሚያቀርቡ መኖራቸውንና እነዚህን በመረጃ ላይ በመመስረትና በማጥራት ካሳ እንዲከፈላቸው የከተማ አስተዳደሩ ወስኖ ወደ ሥራ መግባቱን ያረጋግጣሉ።



ዶክተር አበራ ብሩ



ወይዘሮ አስካለ አያሌው

ፎቶ-እዮብ ተፈራ

**በወቅቱ አንድ ካሬ ከ60 ብር በማይበልጥ ግምት የተሰጣቸው ሲሆን ይህ ግን በአሁኑ ወቅት ማስተካከያ ተደርጎ የግጦሽ ወይንም እርሻ ሲሆን በካሬ ተሰልቶ 1800 ብር ይከፈላል።**

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# የሰው ልጅ የነፍስ ተመን ስንት ነው?

**በቅድሚያ፤**

ርዕሱን የተዋስኩት ጎምቱው የሕግ ምሁር ከጻፉት መጽሐፍ ላይ ነው። ደራሲው በሳል የሕግ ባለሙያ የሆኑት አቶ ሽፈራው ወልደ ሚካኤል ናቸው። ከጀማሪ የሕግ ባለሙያነትና ከሕግ ት/ቤት መምህርነት እስከ የአገሪቱ የፍትሕ ሚኒስትርነት ደረጃ በመድረስ ሕዝባቸውን በቅንነት ያገለገሉት እኚህ አርአያ ሰብ ስለ ማንነታቸውና ስለ አገልግሎታቸው በዚሁ ጋዜጣ ጥቅምት አጋማሽ 2014 ዓ.ም ዕትም ላይ ታሪካቸውና ዜና መዋዕላቸው በሚገባ ተመዝግቦ አንብበናል።

እኚህ የአገር ፈርጥ የሆኑት አባት ለመጽሐፋቸው የሰጡት ርዕስ "የሰው ተመኑ ስንት ነው?" የሚል ነው። ሞጋች ብቻም ሳይሆን ወደ ይዘቱ ጠልቆ እስኪገባ ድረስ ብዙ ግርታ የሚፈጥሩ ጥያቄዎች በአእምሯችን እንዲብላሉ ምክንያት የሆነው ይህ መጽሐፍ ዕድሉ ባላቸው አንባቢያን ቢነበብ ፋይዳው እጅግ ጠቃሚ እንደሆነ ጸሐፊው ምስክርነቱን ይሰጣል።

ይህ ዓምደኛ ለዚህ ጽሑፉ የተዋሰው የመጽሐፉን ርዕስ እንጂ በይዘቱ ላይ ሙሉ ዳሰሳ ወይንም ሥነ ጽሑፋዊ ሂስ ለማድረግ አልተዘጋጀም። እንዳስፈላጊነቱ ወደፊት ጊዜው ሲፈቅድ በይዘቱ ላይ አንዳንድ ሙያዊ ምልከታዎችን ለማድረግ ይሞከራል። ርዕሱን ለመዋስ ሁለተኛው ዋና ምክንያት ታኅሣሥ 1 ቀን 2014 ዓ.ም እኚሁ ደራሲ ከአፍ እስከ ገደፉ ጢም ብሎ ለተሰበሰበ ታዳሚ በመጽሐፉ ርዕስ ላይ በመመሥረት መሳጭና አስተማሪ ንግግር ሲያደርጉ ይህ ዓምደኛም በጉባዔው ውስጥ ተገኝቶ ስለነበር መልዕክቱ ልቡ ውስጥ ጠልቆ ስለገባ ለአንባቢያኑ ማጋራቱ ጠቃሚ መስሎ ስለተያው ነው። ርዕሱንና መሪ ሃሳቡን ላዋሱን ደራሲ ምሥጋናችን ይድረሳቸው።

**የችግሮቻችን አበዛዙ፤ የመፍትሔ ሙከራችን ማነሱ፤**

ይህ ብዕረኛ ለዚህ ታሪካዊ ጋዜጣ ቤትኛና ተባባሪ ዓምደኛ በሆነባቸው ባለፉት 30+ ዓመታት በብዕረ መንገድ ጉዞው ውስጥ ያላነሳቸው ርዕሰ ጉዳዮች ስለመኖራቸው እርግጠኛ ለመሆን ይቸገራል። ከኪነ ጥበባ ሂስ እስከ የዕለት ተዕለቶቹ ሰፋፊ ማሕበራዊ ጉዳዮች፣ ከፖለቲካችን ቱማታ እስከ ኢኮኖሚያዊ ትርታችን፣ ከፍልስፍና እስከ ሃይማኖቶች ፋይዳ፣ ከግል የንባብ ተሞክሮ እስከ የውጭ ጉዞ ዜና መዋዕሎች ወዘተ. በምልከታው ላይ ገደብ ሳያደርግ የብዕሩን ቱሩፋት ለአንባቢያን ያለ ስስት ለማቅረብ ሙከራ አድርጓል።

በእነዚህ ረጅም ዓመታት ውስጥ ይህ ጸሐፊ የተረዳው መሠረታዊ እውነት የፖለቲካችን የግልፍተኝነትና የተለዋዋጭነት ባህርይና አካሄድ ግራ የተጋባ መሆኑንና ግራ እንዳጋባን መኖራችንን በተቀዳሚነት ይጠቅሳል። የኪነ ጥበባቱ ተፈጥሯዊ ሥሪትም አንዴ ጋል አንዴ ቀዝቀዝ የማለት ተፈጥሮ ስላለው ለስክነት ባዕድ መሆኑን ለማስተዋል ማናችንንም አይገድም። በየጊዜው ግርሻው እየተነሳ የሚታመመውና እኛንም ለማይድን ሕመም የዳረገን የኢኮኖሚችን ጉዳይም ዛሬም አልጋ ላይ ወድቆ እያጣጣረና እኛንም ለጣር አሳልፎ በመስጠት እንደ ጀገነ እነሆ የሌማታችንን ባዶነት እያመላከትን አቤት ማለቱን ገፍተንበታል።

አልፎም ተርፎ የዕለት እንጀራችን አዋይ ርቆት ጦም ውለን ጦም ለማደረ እስከ መገደድ ደርሰናል። "ሃይ!" ብሎ የሚያስቆመው አገራዊ ብርቱ የፖሊሲ አቅም መጥፋቱ ለእኛ ዜጎች "ዕንቆቅልህ ምን አውቅልህ" ከማለት ውጭ መፍትሔው ጠፍቶን "የእውር ድመት" ስሜት እንደተሰማን ቀን በመግፋት ላይ ነን።

የብዙኃኑ ሕዝባችን ማሕበራዊ ትሥሥር ድርና ማግ በጥቂት እኩያን ክፉ ድርጊቶች እንዲነትብ የሚደረገው የሌት ተቀን የሴራ ሽረባና ተግባርም መልኩና ገጽታው ከጊዜ ወደ ጊዜ ሲወሳሰብ እንጂ ሲረግብ ለማየት አልታደልንም። የሃይማኖቶቻችንና የሃይማኖት መሪዎቻችን የእምነት ጉልበት ላልቶ ሲልፈሰፈስ እያየንም ፈጣሪን በመሞገት "ለምን? እንዴት?" እያልን በዕለት ጸሎታችንና ሱባዔያችን መሞገታችን አልቀረም።

ከላይ በተዘረዘሩት መልከ ብዙ ጉዳዮች ዙሪያ ይህ ጸሐፊ የዕውቀት አቅሙ የፈቀደውን ያህል ትዝብቱንና ቁጭቱን "መፍትሔ ከሚለው ግምቱና እምነቱ ጋር" ባለመታከት "ይድረስ ለአንባቢያን" እያለ ሲቃትት መኖሩ ለዚህ ጋዜጣ ቤተሰቦች እንግዳ አይሆንም። በዚህ ሁሉ የዓመታት ጉዞው የተማረው ትልቁ ቁም ነገር "ከሞከረነው ይልቅ ያልሞከርነው ነው የሚቆጨን" የሚለው አባባል እውነት መሆኑን ነው።

ከተዘረዘሩት አገራዊ ፈተናዎቻችን በከፋ ሁኔታ ግን ዛሬ ዛሬ እየሰማንና እያስተዋልን ያለነው ወቅታዊው የልብ ስብራታችን እጅግ የመረረ ስለሆነ በእርሱ ጉዳይ ላይ እንደለመድነው የምንቆዝመው የተዋስነውን ርዕሰ ጉዳይ ከሃይማኖታዊ እውነታዎች ጋር በማጎልበት ይሆናል። መቼም ለሰው ልጅ ዋና መጽናኛው ሃይማኖቱም አይደል።

**የተዛነፈው የሰብዓዊነት መስፈርት፤**

ከአሁን ቀደም ለማስታወስ እንደተሞከረው በዘጠና ዘጠኝ ነጥብ ምንትስ መቶኛ ስሌት መሠረት የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ በየሃይማኖቶቹ ጥላ ውስጥ የተጠለለ መሆኑን የስታስቲካችን መረጃዎች በይፋ ያረጋግጡልናል። በአጭሩ "የሃይማኖት የለሽ" ዜጎቻችን ቁጥር እዚህ ግባ የሚባል ባይሆንም እምነት የለንም የሚሉ ግለሰቦችና ቡድኖች ይጠፋሉ ተብሎ ግን አይገመትም። የአምልኳቸው ባህርይና የተመላኪው ምንነት ልዩነት ይኖረው ካልሆነ በስተቀር "ሥጋና ነፍሳቸውን" ያቆራኙበት አንድ "የእኔ" የሚሉት ተመላኪ (ገንዘብ፣ ዕውቀት፣ ጉልበት ወዘተ. ሊሆን ይችላል) ሳይኖራቸው ይቀራል ለማለት ግን ያዳግታል።

በየትኛውም አገርና የዓለም ክፍል የሚገኙ የተጻፉም ይሁኑ ያልተጻፉ ሃይማኖታዊ አስተምህሮዎችና ቀኖናዎች በጋራ ከሚያምኗቸው መሠረታዊ ጉዳዮች መካከል አንዱና ዋነኛው የሰው ልጆች የፍጥረት መነሻ አፈር መሆኑን ነው። ይህ አዳማዊ የአፈር ገላ በፈጣሪ እስትንፋስ ነፍስ መዝራቱና የሕይወቱ ፍጻሜ የሚደመደመውም ከወጣበት አፈር "ግባ መሬቱ!" እየተፈጸመ መሆኑ በጽኑ ይታመናል። ሟቹን በድናቸውን የሚቀብሩትም ሆኑ የሚያቃጥሉ ሃይማኖቶች ይህንን እውነታ በፍጹም አይክዱትም።

የአይሁዶቹና የክርስቲያኖቹ ቅዱስ መጽሐፍ አስረግጦ የሚያስተምረው ይህንኑ እውነታ ነው። እንዲህ በማለት "ያህዌ/እግዚአብሔር አምላክም ሰውን (አዳምን) ከምድር አፈር አበጀው በአፍንጫውም ሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ" (ዘፍጥረት 2፡7) ከአዳም በኋላም የሰው ዘር በሙሉ በአንድ ወንድና ሴት ግንኙነት ሰው ሆኖ በማህፀን ውስጥ መፀነሱ የተገለጸውም እንዲህ ተብሎ ነው።

> **"አቤቱ 'አምላኬ ሆይ!'...በእናቴ ሆድ ውስጥ ሰውረኸኛል፣**
> **ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬያለሁና አመሰግንሃለሁ።**
> **ሥራህ ድንቅ ነው፤ ነፍሴም ታውቀዋለች።**
> **እኔ በስውር በተሠራሁ ጊዜ፣**
> **አጥንቶቼ ከአንተ አልተሰወሩም።**
> **ያልተሠራ አካሌን ዓይኖችህ አዩኝ።**
> **የተፈጠሩ ቀናቴ ሁሉ፣**
> **አንድ እንኳ ሳይቀር በመጽሐፍ ተጻፉ።**
> **(መዝሙር 139፡13-16)።**

በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ተብራርቶ የተገለጸው የሰው ዘር ዘፍጥረትና ወደ አፈር የመመለስ ፍጻሜ ብቻም አይደለም። ከፈጣሪ የተሰጠውን ክብርና ሥልጣንንም በተመለከተ እንዲህ ተጽፏል።

> **"ታስበው ዘንድ የሰው ልጅ ምንድን ነው?**
> **ትጎበኘው ዘንድስ የሰው ልጅ ምንድን ነው?**
> **ከመላእክት እጅግ ጥቂት አሳነስከው፤**
> **በእጆችህም ሥራ ላይ ሾምከው፤**
> **ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዛህለት"**
> (መዝሙር 8)።

ክቡሩ የሰው ልጅ "ከመላእክት ጥቂት ብቻ ያነሰ" ፍጥረታዊ ባህርይ እንዳለው ማረጋገጫውን የሰጠው ቅዱስ መጽሐፍ ስለሆነ ለጥርጥርና ለክህደት የሚጋብዝ አይደለም። እያንዳንዱ የሰው ልጅ የሁሉን ቻይ ፈጣሪ ስሪት ብቻም ሳይሆን "ነፍሱም" የከበረ ዋጋ እንዳላት፤ በከንቱ የሚፈሰው ደሙም ጠያቂና ተሟጋች እንዳለው እውቀት ብቻም ሳይሆን እምነትም ጭምር ነው።

የኢስላም እምነት ቅዱስ መጽሐፍም (ቁርአን) "በአላህ ዘንድ የዒሳ ምሳሌ እንደ አደም ብጤ ነው። ከአፈር ፈጠረው፤ ከዚያም ለርሱ (ሰው) ‹ኹን› አለው። ኾነም።" (ሱረቱ አል-ኢምራን 2፡59) ልክ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ ቁርአኑም ከአዳም በኋላ የቀጠለውን የሰው ዘር መስፋፋት የገለጸው እንደሚከተለው ነው።

"በርግጥም ሰውን ከነጠረ ጭቃ ፈጠርነው። ከዚያም በተጠበቀ መርጊያ ውስጥ የፍትወት ጠብታ አደረግነው። ከዚያም ጠብታዋን (በአርባ ቀን) የረጋ ደም እርገን ፈጠርን። የረጋውን ደም ቁራጭ ሥጋ አድርገን ፈጠርን። ቁራጪንም ሥጋ አጥንቶች አድረገን ፈጠርን። አጥንቶቹንም ሥጋን አለበስናቸው። ከዚያም (ነፍስን በመዝራት) ሌላ ፍጥረት አድረገን አስገኘነው። ከሠዓሊዎችም ሁሉ በላጭ የሆነው አላህ ላቀ" (ሱረቱ አል-ሙእሚኑን 23፡12-14)።

**እናስ የሰው ልጅ የዋጋ ተመኑ ምን ያህል ይሆናል?**

ከላይ የተዘረዘሩትን የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች አብዝተን ለማስታወስ የተገደድነው ወቅታዊው የአገራችን የንጹሐን ዜጎች ጭፍጨፋ ጉዳይ በፖለቲካውም ሆነ በማሕበራዊ አረደዳችን ላይ እጅግ ግራ ስላጋባን ነው። በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የዜጎችን ደም በከንቱ የሚያፈሱ "የደም ጥማተኞች" ቁጥርና ዓይነት እንዲህ ነው ብሎ መዘርዘሩ አዳጋች የሆነ ደረጃ ላይ መድረስ ብቻም ሳይሆን እንደ አገር "ለዛሬ ብቻም ሳይሆን ወየው ለነገ ትውልዳችን!" እያልን መቃተት ከጀመርን ሰነባብተናል።

በዚህን መሰሉ የንጹሐን ዜጎች ጭፍጨፋ ላይ የተሰማሩት "ዱር አደር" አሸባሪዎችና ሽፍቶች እንደ አሸን የመብዛታቸው ዕንቆቅልሽ መፍትሔ ለማሰብ እስከምንቸገር ድረስ ነገሮች እንደ ተወሳሰቡን ጀንበሯ መሽታ እየጠባች ነው። ለመሆኑ በፈጣሪ የፍጹም ከሃሊነት ጥበብና እውቀት የተፈጠረን የሰው ልጅ እንደ ተራ የመስዋዕት እንስሳ ሕይወቱን ሲነጥቁት፣ በአልባሌ አገዳደል እስትንፋሱን ሲያጨልሙና ግድያውን ሲያስተባብሩ በደም የጨቀየው እጃቸው አይንቀጠቀጥም? በእብሪት ሞራ የተደፈነው ኅሊናቸውስ አይወቅሳቸውም?

የሰው ልጅ የነፍሱ ተመን የሚለካውና የሚቆጠረው በሰው ሠራሹ ቋንቋ፣ ባህል ወይንም በዘሩ ማንነት እየተሰፈረ ሳይሆን የሕያው ፈጣሪ እስትንፋስ እንዳለበት በማመን ሊሆን በተገባ ነበር። ለሰው ልጅ ሰው ሆኖ መፈጠር አንዳችም አስተዋጽኦ የማድረግ አቅምም ሆነ ክህሎት የሌለው ራሱ አፈር የተሸከመ ሟች ሰው እንዴት ወገኑን በግፍ እየጨፈጨፈ እንደ ጀግና ፎክሩልኝ፣ አቅራሩልኝ፣ አዳምቁልኝ እያለ እርኩስ ድርጊቱን በአደባባይ ሊገልጥ ድፍረት ሊያገኝ ቻለ? ምሥጢሩስ ምን ሊሆን ይችላል።

የፖለቲካ የበላይነት ለማግኘት?፣ የኢኮኖሚውን ቀኝ እጅ ለመጨበጥ?፣ በማሕበረሰቡ ውስጥ ጀግና ተብሎ የተለየ ክብር ለማግኘት? ዘሩና ብሔሩ ወይንም ቋንቋውና ባህሉ የተሻለ ሆኖ እንዲቆጠርለትና እንዲገንለት ለማድረግ? ወዘተ. ይህ ሁሉ ምኞቱና ግቡ ከንቱ የከንቱ ከንቱ እንደሆነና "የተሸከመው አፈር ወደ አፈር ሲቀላቀል" በፈጣሪ ፍርድ ተገቢውን የግፍ ዋንጫ እንደሚጎነጭ ሊረዳውና ሊገባው ይገባል። "የማታውቁ ከሆነ የእውቀት ባለቤቶችን ጠይቁ" የሚለው ኢስላማዊ ጥቅስ እዚህ ቦታ ቢታወስ አግባብ እንደሆነ ይታመናል።

**እናጠቃለው፡-** የሰው ልጅ ነፍስ በሰብዓዊ ፍጡር የዋጋ ተመን የሚለካና የሚመዘን አይደለም። የነፍሱ ባለቤትና ፈጣሪ አምላክ ራሱ ብቻ ነው። እንኳንስ የፈጣሪ ዋና ጉዳይ የሆነው የሰው ልጅ ቀርቶ ሌሎች የቤት ቁሳቁሶችም ቢሆኑ ባለቤትና "የእኔ" ባይ አላቸው። "የሰው ደም የሚያፈስ ሁሉ ደሙ ይፈሳል። ሰውን በእግዚአብሔር መልክ ፈጥሮታልና" (ዘፍጥረት 9፡6)። ይህ ጠቅላይ ሃሳብ ለፍርድም ለተማጽኖም በእጅጉ በቂና ከበቂ በላይ ነው። በሌላ አቀራረብ ይገባቸው ከሆነ ለገዳዮቹም ሆነ ለአስገዳዮች የሚጠቅም አንድ አገራዊ ብሂል እናስታውሳቸው፤ "በጎች ተደጋግመው የሚበሉ ከሆነ ችግሩ ከተኩላው ሳይሆን ከእረኛው መሆኑን መጠርጠሩ አይከፋም"።

**ሰላም ይሁን።**

# በአቅርቦት እጥረትና በሰው ሰራሽ ችግር የታነቀው የስኳር ግብይት

**ፍሬሕይወት አወቀ**



በአገሪቷ እየታየ ያለውን የስኳር እጥረት ተከትሎ መንግስት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለሸማቾች የሚያቀርበውን ስኳር መጠን እየቀነሰ ይገኛል። በገበያ ላይ ያለው የስኳር ዋጋም አልቀመስ እያለ ነው። በአዲስ አበባ ከተማ ለአንድ ስኒ ቡና እንዲሁም ለአንድ ብርጭቆ ሻይ እየተጠየቀ ያለው ዋጋም የስኳር ገበያው ችግር ውስጥ መሆኑን ያመለክታል። አስር ብር ይሸጥ ለነበረው አንድ ስኒ የጀበና ቡና አሁን ከ15 እስከ 20 ብር እየተከፈለ ይገኛል፤ የአንድ ብርጭቆ ሻይ ዋጋም በተመሳሳይ ከ10 እስከ 15 ብር ነው ሲሉ ሸማቾች ይጠቁማሉ። የዚህ ምክንያቱ የስኳር አቅርቦት እጥረትና ዋጋ መናር መሆኑን ነው የሚገልጹት።

በቅርቡ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የ2015 ዓ.ም የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸሙን ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የንግድና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ባቀረበበት ወቅት በ2015 ዓ.ም ከውጭ ተገዝቶ መግባት የነበረበት የስኳር ምርት ወደ አገር ውስጥ አለመግባቱን አስታውቋል፤ በመንግሥት መጋዘኖች ለመጠባበቂያ የሚሆን የስኳር ምርት አለመኖሩንም ገልጾ፣ ይህ ሁሉ በአገሪቱ እየታየ ላለው የስኳር እጥረትና የገበያ ችግር እንደ ምክንያት እንደሚጠቀስ ተጠቁሟል።

መንግሥት በሩብ ዓመቱ ከ835 ሺ በላይ ኩንታል ስኳር ለማሠራጨት አቅዶ እንደነበረ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትሩ አቶ ገብረ መስቀል ጫላ አስታውቀው፣ ያሰራጨው ግን 284 ሺ ኩንታል ብቻ መሆኑን ተናግረዋል። በሌላ በኩል በፍራንኮ ቫሉታ ከታክስና ከቀረጥ ነፃ አንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል ስኳር ወደ አገር ውስጥ እንደገባም ተጠቅሷል።

ይሁን እንጂ መንግሥት ለማህበረሰቡ የሚያቀርበው የስኳር መጠን በአሁኑ ወቅት እጅግ ያነሰ መሆኑን ተከትሎ ከፍተኛ የስኳር እጥረት ተከስቷል፤ በሸማቾች ማህበራት አማካይነት ለማህበረሰቡ እየቀረበ ያለው የስኳር መጠን በእጥፍ መቀነሱ ይታወቃል። ከሸማቾች ማህበራት መደብሮች ውጭ ባለው ገበያም አንድ ኪሎ ስኳር ከ120 ብር እስከ 130 ብር እየተሸጠ ነው።

በስኳር አቅርቦት እጥረቱና እየታየ ባለው የዋጋ ጭማሪ ዙሪያ ያነጋገርናቸው የምጣኔ ሃብት ባለሙያው ዶክተር ተሾመ አዱኛ በቅድሚያ ስለገበያዎች የተለያየ ባህሪ አብራርተዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ ገበያዎች የተለያየ ባህሪ አላቸው። ነጻ የኢኮኖሚ ገበያ፣ ሞኖፖሊ ገበያና መሐል ላይ ያሉ የገበያ አይነቶች አሉ።

ገበያዎች በራሳቸው የሚንቀሳቀሱ አይደሉም። የተለያዩ አካላት ከጀርባቸው አሉ። እነዚህ አካላት አቅራቢዎችና ሸማቾች ሲሆኑ፣ የገበያውን ውጤት መወሰን የሚችሉ ናቸው። የሸማቾችና የአቅራቢዎች ባህሪ ደግሞ የገበያዎችን ውጤት እንደሚወስን ዶክተር ተሾመ ጠቅሰው፣ ገበያ ውስጥ ያሉ ሸማቾች መጠንና የአቅራቢዎች መጠንም እንዲሁ ገበያውን መወሰን እንደሚችሉ ነው ያብራሩት።

በኢትዮጵያ ያለው የገበያ ሁኔታም ይህንኑ እንደሚያመለክት ነው የተናገሩት፣ ለስኳር አቅርቦት እጥረቱ እንዲሁም ለዋጋው መናር ምክንያቱ ገበያው የሚመራበት ስርዓት የሌለው ከመሆኑ ጋር እንደሚያያዝ አስታውቀዋል።

በአገር ውስጥ የሚገኙ ስኳር አቅራቢዎች ጥቂት እንደሆኑም ዶክተር ተሾመ ጠቅሰው፣ ውስን በመሆናቸው ሰው ሰራሽ የዋጋ ንረት ለመፍጠር የተጋለጡ መሆናቸውን ይናገራሉ። ይህም የተዛባ ስርጭት እንዲኖር ማድረግ ያስችላቸዋል ይላሉ። ከዚህ ባለፈም ተጠቃሚው ለገበያ የሚሰጠው ምላሽ ወይም የሚያሳየው ባህሪ ገበያው እንዲበላሽ የሚያደርግ መሆኑንም ይጠቁማሉ።

የኢትዮጵያ ሸማች ወይም ደንበኛ ዋጋ ይጨምራል በሚል ስነልቦና የተገነባ መሆኑን ጠቅሰው፣ ከዚህም ባለፈ ዋጋው ቢጨምርም እገዛዋለሁ እንጂ፤ እተወዋለሁ የሚል ስነልቦና እንደሌለው ያስረዳሉ። በመሆኑም አቅራቢው ውስን በመሆኑ ከሚፈጥረው ሰው ሰራሽ የዋጋ ንረት በተጨማሪ በሸማቹ ማህበረሰብ ዘንድ ያለው ስነልቦና ዋጋ ይጨምራል የሚልና ቢጨምርም እገዛዋለሁ የሚል መሆኑ ተዳምሮ አቅርቦት ቢኖርም ዋጋ የሚጨምርበት ሁኔታ እንዳለ ነው ያብራሩት።

ሌላው የምጣኔ ሃብት ባለሙያ አቶ ወሰንሰገድ አሰፋ የስኳር እጥረትና ዋጋ መወደድን አስመልክቶ ያነሱት ሀሳብ የዶክተር ተሾመን ሃሳብ የሚያጠናክር ነው፤ አሁን በስኳር ምርት ላይ እየታየ ያለው የዋጋ ንረት ከምርት እጥረት ጋር ተያይዞ የመጣ ነው ለማለት እንደሚያስቸግር አቶ ወሰንሰገድ ይገልጻሉ። እጥረት ስለመኖር አለመኖሩ ለማወቅ ጥናት እንደሚያስፈልግ ጠቁመው፣ ገበያው ግን ሰው ሰራሽ በሆነ እጥረት እየተረበሸ ስለመሆኑ አመላካቾች መኖራቸውን ይጠቅሳሉ። አንድ ነገር የእውነትም እጥረት ሲገጥመውና ሳይኖር ሲቀር የሚፈጠር እጥረትና ምርቱ እያለ ሰው ሰራሽ በሆነ ችግር ምክንያት የሚፈጠር እጥረት ስለመኖሩም አስረድተዋል።

እጥረቱን ለማብራራትም በአገሪቱ እየተባባሰ የመጣውን የሲሚንቶ እጥረት በአብነት ይጠቅሳሉ፤ የሲሚንቶ እጥረት እየተከሰተ ያለው በአገሪቱ ሲሚንቶ እየተመረተ ባለበት ሁኔታ መሆኑን ይጠቅሳሉ። አንድን ምርት የተወሰኑ ሰዎች በብዛት ያከማቹትና ገበያ ውስጥ ሰው ሰራሽ እጥረት ሲከሰት ጠብቀው ያወጡታል። ሰው ሰራሽ እጥረቱ ደግሞ ዋጋው እንዲንር ያደርጋል። በዚህም ህዝቡን ይበዘብዙታል ሲሉ አቶ ወሰንሰገድ ያብራራሉ። ምናልባትም በተመሳሳይ በስኳር ላይ ሰው ሰራሽ እጥረት ተከስቶ ሊሆን እንደሚችልና ገበያ ላይ እየታየ ያለውም ተመሳሳይ ነገር ስለመሆኑ አመላካቾች እንዳሉ ይጠቁማሉ። በሲሚንቶ ላይ ሰው ሰራሽ ችግር እንደተፈጠረ ሁሉ በስኳር ምርት ላይም ህገወጥ ንግድ እየተካሄደበት እንደሆነ በመረጃ ባይደገፍም አመላካች ነገሮች እንዳሉ በመጥቀስ፣ ችግሩን መለየትና መፍትሄ ማስቀመጥ ይገባል ብለዋል።

ዶክተር ተሾመም ችግሮቹን መለየት አስፈላጊ መሆኑን ነው ያመለከቱት፤ በስኳር ምርትና የገበያ ሂደት ላይ ያለውን ችግር ለመፍታት በቅድሚያ መረጃን መሰረት ባደረገ መልኩ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ችግሩን ማጥናት እንደሚገባ ያመለክታሉ። ገበያውን መክፈትና ነጻ ማድረግም ያስፈልጋል ባይ ናቸው። ገበያው ነጻ መሆን አለበት ሲባልም አዳዲስ ስኳር ማምረቻ ፋብሪካዎችን ከመክፈት ባሻገር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የውጭ አገር ኢንቨስትመንትም መግባት እንዲችል መፍቀድ ያስፈልጋል ሲሉ አብራርተዋል።

ዶክተር ተሾመ እንደሚሉት፤ የስኳር ማምረቻ ቴክኖሎጂ በጣም ትልቅ ቴክኖሎጂ ነው፤ የስኳር ምርት በባህሪው ከተለያዩ የእሴት ሰንሰለቶች ጋርም ይገናኛል። ለአብነትም ስኳር ለማምረት አስቀድሞ ሸንኮራ አገዳ መትከል ያስፈልጋል፤ ይህም ከመሬት ጋር ይገናኛል። ስኳር ከፍተኛ ቴክኖሎጂ የሚጠይቅ እንደመሆኑ ይህንኑ መሰረት ያደረገ የውጭ አገርና የአገር ውስጥ ኢንቨስትመንት እንዲገባ መፍቀድን ይጠይቃል።

ዶክተር ተሾመ ችግሩን ለመፍታት የገበያውን ሂደት ተጠያቂነት ባለበት መንገድ መምራት እንደሚያስፈልግ ያመለክታሉ። አሁን ያለው የገበያ ሁኔታ እኛ ገበያውን መምራት ሲገባን በተቃራኒው ገበያው እኛን እየመራ መሆኑን የሚያመለክት ነው ይላሉ። ይህ በሁሉም አካባቢ መስተካከል እንደሚገባውም ተናግረዋል። ለዚህም የገበያ መረጃዎችን ማስተካከል፣ የገበያ ማእከላትን ማስፋፋት እንደሚያስፈልግ፣ የስኳር አቅራቢዎች መጠናከር እንዳለባቸውና በስኳር አቅርቦት ስም የሚታዩ የኪራይ ሰብሳቢነት ተግባራት ሊወገዙ እንደሚገባ አመላክተዋል። እንደ መድሃኒትና መሰል ምርቶች ሁሉ ለስኳር ዋጋ ተመን ቢወጣለት የተሻለ እንደሆነም አስገንዝበዋል።

በአምራችና በተጠቃሚው መካከል ያለው ልዩነት መጥበብ እንዳለበትና በአምራቹና በተጠቃሚው መካከል ያሉትን አካላት ማስወጣት ሌሎች መፍትሔዎች መሆናቸውን የጠቆሙት ዶክተር ተሾመ፤ እነዚህና መሰል ችግሮችን በማስወገድ ስኳሩ ከአምራቹ ወደ ተጠቃሚው በቀጥታ መድረስ እንዲችል ማድረግ ከተቻለ በአገሪቱ እየታየ ያለውን የስኳር አቅርቦት እጥረት መፍታትና ገበያውን ማረጋጋት እንደሚቻል ያብራራሉ።

ሌላው በዘርፉ ያለው የቅንጅት ችግር መሆኑንም ይጠቅሳሉ። ወደ ማምረት ስራ ይገባሉ የተባሉ የስኳር ማምረቻ ፋብሪካ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ መጠናቀቅ አለመቻላቸው አንዱ የቅንጅት ችግር መሆኑን በአብነት ይጠቅሳሉ። በተቀናጀ መንገድ አለመስራትና የግብዓት አቅርቦት ችግር እንዳለም ገልጸው፣ የአገር ውስጥ ባለሃብቶች አቅም ማነስና ወደ ዘርፉ አለመግባት በዚህ ላይ ተደማምሮ አቅራቢ የተባሉት የተወሰኑ አካላት ዋጋውን እንደፈለጉ ማውጣት እንዲችሉ መንገድ ከፍቷል ይላሉ።

በአገሪቱ ስኳር የሚቀርበው በመንግሥት እና በነጋዴ መሆኑን ጠቅሰው፣ ነጋዴው መንግሥት ከሚያቀርበው በእጥፍ እየሸጠ እንደሚገኝ ተናግረዋል። ሸማቹ ከመንግሥት ያላገኘውን አንድ ኪሎ ስኳር ከ120 እስከ 130 ብር ከነጋዴው የሚገዛበትን ሁኔታ መፈጠሩን ገልጸው፤ ይህም ገዢ ስላለ መሆኑን አስረድተዋል። ነጋዴው ስኳሩን በየትኛውም መንገድ ወደ አገር ውስጥ ገበያ የሚያስገባው የነጋዴው ባህሪ እንዳለ ሆኖ አንድ ኪሎ ስኳር በ130 ብር ለመግዛት ፈቃደኛ የሆነ ሸማች በመኖሩ መሆኑን ያብራራሉ። ይህ መሆን አልነበረበትም፤ ችግሩ ያለው ሸማቹና አቅራቢው ዘንድ ነው ብለዋል።

ይህን አይነቱን የገበያ ሁኔታ መንግሥት ማስቀረት እንደማይችልም ዶክተር ተሾመ አመልክተው፣ ለእዚህ ምክንያቱ ደግሞ በመንግሥት በኩል ብዙ ስርዓቶች አለመኖራቸው ነው ይላሉ። በመንግሥት በኩል ያለው ስርዓት አድርግ አታድርግ የሚል አስተዳደራዊ ስርዓት መሆኑን ገልጸው፣ በገበያው በኩል ግን ገበያውን ሊያስተካክሉም ሆነ ሊያበላሹ የሚችሉ የተለያዩ ስርዓቶች እንዳሉ ይናገራሉ።

አቶ ወሰንሰገድ ለስኳር ዋጋ መናር አንደኛው ምክንያት የፍላጎት መጨመር መሆኑን ይጠቅሳሉ። ከዚህ ቀደም ማህበረሰቡ ስኳር የሚጠቀመው ለሻይ እና ለቡና እንደነበር አስታውሰው፣ አሁን ማህበረሰቡ ስኳርን በተለያዩ ምግቦች ላይ መጠቀም መጀመሩ ለእጥረቱ አንድ ምክንያት እንደሆነ ያመለክታሉ። ይህም ፍላጎቱ እንዲጨምር የራሱ ድርሻ እንዳለው ተናግረዋል። በአገሪቱ ያለው አቅራቢ በማምረት ሳይሆን በዋጋ ከፍተኛ ጥቅም ማግኘት የሚፈልግ መሆኑም የስኳር ዋጋ የተጋነነ ዋጋ እንዲኖረው ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ መሆኑን ጠቅሰዋል።

እንደ አቶ ወሰንሰገድ ገለጻ፤ አቅራቢው ምርት ላይ ሳይሆን ዋጋው ላይ ነው ትኩረት የሚያደርገው። ይህም ሰው ሰራሽ የዋጋ ንረት እንዲፈጠር አድርጓል። ብዙ ሰዎች ደግሞ ዋጋ ሲጨምር የምርት እጥረት እንዳለ ታሳቢ በማድረግ በስፋት ለመግዛት ጥረት ያደርጋሉ።

የዚህ አንዱ መፍትሄም ማህበረሰቡ ዋጋ የሚጨምረው የግድ እጥረት ስላለ አለመሆኑን በመገንዘብ እጥረት ሳይፈጠር ዋጋ የሚጨምሩ አካላት እንዳሉ በመገንዘብ በተጋነነ ዋጋ ከመግዛት መቆጠብ አለበት ሲሉ ያስገነዝባሉ። አቅራቢውም ዋጋ ላይ ሳይሆን ምርት ላይ ትኩረት አድርጎ ቢሰራ ሰው ሰራሽ የዋጋ ንረትን ማስወገድ ይቻላል ብለዋል።

በኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ የኮርፖሬት ጉዳዮች ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ዘመድኩን ተክሌ በቅርቡ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት፤ ከስኳር ጋር የተያያዘው ችግር መከሰት የጀመረው ከ2003 ዓ.ም አንስቶ መሆኑን ይገልጻሉ። ችግሩ እየተንከባለለ ባለፈው ዓመት አስደንጋጭ ደረጃ ላይ መድረሱን ምክትል ዋና ስራ አስፈጻሚው ጠቅሰው፣ በዚህ ዓመትም የስኳር ችግሩ ተባብሶ መቀጠሉን አስታውቀዋል። ለችግሩ መባባስም ፋብሪካዎች በየዓመቱ ምርታቸው እየቀነሰ መምጣቱ አንዱ ምክንያት መሆኑን ተናግረዋል። ከፍተኛ የስኳር መጠን ያመርት የነበረው ፊንጫ ስኳር ፋብሪካ በፀጥታ ችግር ማምረት አለመቻሉ ሌላው ምክንያት ነው ብለዋል። በተያያዘም መተሐራ ላይ አንድ ሺ ሄክታር የአገዳ ማሳ በጎርፍ መጥፋቱ ሌላው ችግር እንደሆነ መጥቀሳቸው ይታወሳል።

በአገሪቱ እየታየ ካለው የስኳር አቅርቦትና ፍላጎት ከፍተት ችግርን ለመፍታት በ2020 ዓ.ም ከውጭ የሚገባውን ስኳር ሙሉ ለሙሉ በአገር ውስጥ ምርት ለመተካት ስትራቴጂ ተነድፎ እየተሰራ መሆኑንም ኮርፖሬቱ ማስታወቁ ይታወሳል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ በእድገትና ትራንስ ፎርሜሽን ሁለት የእቅድ ዘመናት 10 የስኳር ፋብሪካዎችን በመገንባት በነባሩቹም ላይ ማስፋፊያዎችን በማድረግ የአገሪቱን የስኳር ፍላጎት ከማሟላት ባሻገር ስኳር ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ ግንባታዎች ተጀምረው እንደነበር ይታወቃል። የአዳዲሶቹ ፋብሪካዎች የግንባታ መጓተት አጋጥሟቸው እንደነበር ይታወሳል፤ የለውጡ መንግስት ግንባታቸውን ለማጠናቀቅ ባደረገው ጥረት የተወሰኑት ወደ ማምረት ገብተዋል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ መንግስት አንዳንድ ስኳር ፋብሪካዎችን ለግሉ ዘርፍ ለማስተላለፍ እየተሰራ ይገኛል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ገበያን ፍላጎት ይመራዋል

**ዋስልኝ አየለ**

ገበያን ፍላጎት ይመራዋል፤ አቅርቦት ደግሞ ፍላጎትን ይከተላል የሚባል የኢኮኖሚ ሰዎች ሀሳብ አለ። በእርግጥ ይህን ለማወቅ የኢኮኖሚስት ባለሙያ ድረስ አያስኬድም። ለማንም ተራ ግለሰብ ሁሉ ግልጽ ነው።

አንድ ነጋዴ ዕቃ የሚያመጣው የሚሸጥለትን ነው። ደንበኞቹ በተደጋጋሚ ‹‹... አለህ?›› የሚሉትን ዕቃ ያመጣል። በተመሳሳይ አቅራቢም እንደዚያው፤ የሚፈልገውን ነገር ነው የሚያቀርብ።

ይህን ነገር ያነሳሁት ስለ ኢኮኖሚ ልተነትን አይደለም። ይልቁንም ከሰሞኑ የታዘብኩትን ከዚህ ጋር ለማመሳሰል ነው።

ነፍሱን ይማረውና ተወዳጁን አርቲስት ታሪኩ ብርሃኑ (ባባ) በዚህ ሳምንት በሞት አጥተናል። ታዲያ ታዋቂ ሰው በሞተ ቁጥር አንድ የሚደጋገም አሰልቺ ነገር ቢኖር የ‹‹ዩትዩቦች›› የማጭበርበሪያ አሉባልታ ነው። ታዋቂ ሰው በሞተ ቁጥር ዋና ጉዳይ የሚሆነው እነርሱ የሚፈጥሩት የሀሰት አጀንዳ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ለለቅሶ የሚሄደውን ሀዘንተኛ የግል ገመና ሁሉ ሳይቀር ለገበያ ማቅረብ ነው። ማን ሳቀ ማን አለቀሰ የሚል ግምገማ ሁሉ ሳይቀር ይካሄዳል። ይህ ቅጥ ያጣ ሥራቸው በታሪኩ ብርሃኑ የአስከሬን ሽኝት ስነ ሥርዓት ላይ ጭራሹንም እንዳይገቡ አስደረጋቸው።

ዋናው ጥያቄና ትዝብት ግን ይህ ለምን ሆነ? የሚለው ነው!

መግቢያ ላይ እንዳልኩት ነው። ዩትዩበሮችን እንደ ነጋዴ እንያቸው። እኛ ደግሞ ሸማች (ደንበኛ ነን)። እያቀረቡልን ያሉት የምንፈልገውን ነገር ነው። በእርግጥ አንድ ነጋዴ ጥራት የሌለው ዕቃ ወይም ጎጂ የሆነ መርዛማ ነገር ሲሸጥ ይጠየቃል። በዚህ መሰረት አገርና ሕዝብ የሚጎዳ ነገር የሚያቀርቡት የዩትዩብ ሻቃዮች መጠየቅ ነበረባቸው። እስከዚያ ድረስ ግን የእኛን የሸማቾችን ችግር ልብ እንበል!

ከእውነተኛ ነገር ይልቅ ለአሉባልታ አይደለም ወይ ቅድሚያ የምንሰጠው? አንድ የሕክምና ዶክተር ስለአንድ ገዳይ በሽታ የሚያብራራ ቪዲዮ ቢለቀቅ እና ‹‹የታሪኩ ብርሃኑ አሟሟት ምሥጢሮች›› የሚል ቪዲዮ ቢለቀቅ የትኛው ነው ብዙ ተመልካች የሚያገኘው ?

ሕይወታችንን የሚያድን ሙያዊ ማብራሪያ ከሚሰጠው ሐኪም ይልቅ የሌላ ሟች የአሟሟት ሁኔታ ምን ይሆን የሚለው ያሳስበናል። ይሄ መጥፎ ልማዳችን ነው።

ግዴለም! ምሥጢራዊ ነገሮችን ለማወቅ መጓጓት የሰው ልጅ ባህሪ ነው እንበል! ቢያንስ ግን የዩትዩብ ተደጋጋሚ ውሸት ግልጽ ማጭበርበሪያ መሆኑ እየታወቀ እንዴት ሰው ደጋግሞ ይሸወዳል? እንደዚያ የሚያደርጉት እኮ ውሸት መሆኑን እያወቅንም ቢሆን ስለምናይላቸው ነው።

ኢትዮጵያ ቴሌቪዥንን ወይም ፋና ወይም ዋልታ ወይም ሌላ ‹‹ሜይንስትሪም›› ሚዲያ እንደዚያ አይነት ርዕስ ቢሰጥ ምናልባት የምርመራ ዘገባ ሰርተው ነው በሚል ያጓጓል፤ ሀሰት ቢሆን እንኳን ግልጽ የሆነ ተጠያቂነት ያለባቸው እና ለመውቀስም ባለቤት ያላቸው ስለሆኑ አያደርጉትም ብለን እናምናለን። በአጠቃላይ መረጃውን ለማየት እንገደዳለን።

ሰው እንዴት በአንድ ግለሰብ የሚመራ፣ የኤዲቶሪያል ሕግ የሌለው፣ ለአገር ግንባታ ሳይሆን ለግለሰብ ሳንቲም መልቀሚያ ተብሎ የተከፈተ የማህበራዊ ሚዲያ ገጽ ይሸውደዋል ? የዚያ ገጽ (ቻናል) ባለቤት እኮ ግለሰብ ነው። በአንድ ግለሰብ ስሜት ብቻ የሚመራ ነው። ስለዚህ ብዙ ተመልካች ያስገኝልኛል ያለውን ነገር ሁሉ ያደርጋል።

እዚህ ላይ ግን በኃላፊነት የሚሰሩ የሉም ማለቴ አይደለም። ፈቃድ አውጥተው፣ ብቁ ባለሙያዎችን ቀጥረው፣ በትልልቅ መገናኛ ብዙኃን የብዙ ዓመት ልምድ ያላቸው ጋዜጠኞች የሚሰሩባቸው የዩትዩብ ቻናሎች መኖራቸውን አምናለሁ። እነርሱ እንዲህ አይነት የበሬ ወለደ ዜና አይሰሩም፤ እያወራሁ ያለሁት ተመልካች ለማግኘት ብቻ ብለው ስለሚያጭበረብሩት ነው።

ሲጀመር በተገቢው የጋዜጠኝነት ሙያ የሚሰራ ዜና የሚጮህ ርዕስ የለውም። አንድ የዜና ርዕስ ጫጫ ከሆነ የውሸት ወይም የተጋነነ የመሆኑ ምልክት ነው። አርዕስተ ዜና ይዘቱን ጠቅልሎ የሚነግር ጥቅል ርዕስ ነው። በዜናው ውስጥ የማይገኝን ነገር መግለጽ የለበትም። በዩትዩብ ውስጥ ግን እንዲህ አይነት የነጭ ውሸት ርዕሶች የተለመዱ ሆነው ሳለ በተደጋጋሚ የሚሸወዱ ሰዎች ናቸው የሚያሳዝኑት።

በበኩሌ በዩትዩብ ርዕስ ተሸውጄ አላውቅም። ገና ርዕሱን አይቼ ነው የሚገባኝ። ‹‹አዳምና ሔዋን ከገነት ሲባረሩ ለማየት ሊንኩን ይጫኑ›› አይነት የማይመስሉ ነገሮችን ለማየት ደቂቃ አላባክንም። ምክንያቱም ቀደም ሲል እንዳልኩት እውነተኛ ነገር ጫጫ ርዕስ አይጠቀምም።

ሚዲያን የመከታተልና የማወቅ ልማዳችን ለማጭበርበር ምቹ ነው። የውሸት ርዕስ የሚጠቀሙ ሰዎች ሌላ የተለየ ዓላማ ኖሯቸው ሳይሆን ሳንቲም ለማግኘት ነው። የፖለቲካ ዓላማ ያላቸው በሚፈጠረው ውዥንብር የሚጠቀሙት ነገር ስላለ ነው። እነዚህኞቹ ግን በተመልካች ብዛት ክፍያ እንደሚገኝ ስለሚያውቁ ለክፍያው ነው። ለፖለቲካ አጭበርባሪዎችም ሆነ ለሳንቲም አጭበርባሪዎች ምቹ ሁኔታ የፈጠረላቸው ግን ተመልካቹና ተከታዩ ነው።

መነሻዬ የአርቲስት ታሪኩ ብርሃኑ (ባባ) ሕልፈት ነውና በዚሁ እግረ መንገድ ሌላም ትዝብት ላንሳ። ብዙዎች ‹‹በሕይወት እያለ ነበር ማገዝ የነበረባችሁ›› እያሉ ሀዘናቸውን የሚገልጹ ሰዎችን ይወቅሳሉ። ለሞት የተዳረገው እነዚህ ሀዘናቸውን የሚገልጹ ሰዎች ባለመርዳታቸው ነው እያሉ ይወቅሳሉ።

አዎ! ሰውን ማገዝ ያለብን በሕይወት እያለ ነበር፤ ዳሩ ግን አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በአጋዥ ብዛት የማይተርፍ ሕይወትም አለ። በአጋዥ እጦትም ሆነ ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ሰው ከሞተ ያላገዘ ሰው ሀዘኑን አይግለጽ አይባልም። በዚያ ላይ በአንድ ታዋቂ ሰው ሞት ጥልቅ ሀዘን የተሰማው ሁሉ ሰውየውን የማገዝ ዕድል አለው ማለት አይቻልም። ማገዝ ማለት የግድ በገንዘብ ብቻ እንዳልሆነ ግልጽ ነው፤ ሰው በቻለው ሁሉ ያግዛል። ዳሩ ግን የሰውየው ሕይወት ለብዙዎች ግልጽ ላይሆን ይችላል። ሰውየው የሞተው መታከሚያ አጥቶ ነው? ከጎኑ የሚሆን ሰው አጥቶ ነው? የሚለውን የሚያውቀው በጣም ቅርብ የሆነ ሰው ብቻ ነው። አንድ የማደንቀው አርቲስት በድንገት መሞቱን ስሰማ ልደነግጥና ሀዘኔን ልገልጽ እችላለሁ፤ ቀደም ብየ ማገዝ ነበረብኝ ለማለት ግን ምን ሁኔታ ላይ እንዳለ የማውቅ ከሆነ ብቻ ነው።

ይሄ ሁሉ ወቃሽ ይህን ያህል ከተቆጨ አሁንም አጋዥ አጥተው የሞት አፋፍ ላይ ያሉ አሉና እነርሱን በማገዝ አዲስ ልማድ መፍጠር ይቻላል። እርግጥ ነው በዚህ በኩል እንኳን አንታማም፤ ኢትዮጵያውያን መረዳዳት የምርም ባህላችን ነው። ይሄ ሁሉ እርዳታ ፈላጊ እያለ እንኳን ሰጪ አለ። ዳሩ ግን ‹‹በሽታውን ያልተናገረ መድሃኒቱ አይገኝለትም›› እንደሚባለው ችግሩ ሳይታወቅ ሕይወቱ ያለፈ ሰው ግን አድናቂዎቹ ምንም ማድረግ አይችሉም።

መነሻዬ በሀሰት ዜና ብዙ ተመልካች የሚያገኙ ናቸውና መደምደሚያየም እሱ ነው። ከቁም ነገር እና በመረጃ ከተደገፉ ፕሮግራሞች በላይ አሉባልታና ውሸት የምንወድ ከሆነ የምንፈልገውን ነው የሚያቀርቡልን፤ አሉባልታ ደግሞ የመውጣትና መውረድ ልፋት አይጠይቅም፤ ስለዚህ እንዲህ አይነት ደላላዎችን መቅጣት የሚቻለው ባለመከታተል ነውና እኛው ልክ እናስገባቸው!

# ዓለም አቀፍ




## የናይጄሪያ ምርጫ ጣቢያዎች የታጣቂዎች ዒላማ እየሆኑ ነው

**በጋዜጣዉ ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡ የአገሪቱ ምርጫን ለማስተጓጎል የቦኮሃራም ታጣቂዎች ምርጫ ጣቢዎች ላይ ያነጣጠረ መጠነ ሰፊ ጥቃት እያደረሱ መሆናቸው ቢቢሲ ዘገበ።

በሰኞ እለት በደቡብ ምስራቅ ናይጄሪያ በኢሞ ግዛት በሚገኘው ምርጫ ኮሚሽን ሕንጻ ላይ ታጣቂዎቹ ባደረሱት ጥቃት አንድ ፖሊስ ጨምሮ ቢያንስ አራት ሰዎች ሕይወታቸውን አጥተዋል።

ኮሚሽኑ በመጪው የካቲት በሚካሄደው የአገሪቱ ጠቅላላ ምርጫ ለማሳካት የቋሚ መራጮች የምርጫ ካርድ ለአዳዲስ ተመዝጋቢዎች ለመበተን ዝግጅት እያደረገ ባለበት ሁኔታ ላይ ጥቃቱ የተከፈተው። በአንድ ሳምንት ውስጥ በይሄንኑ ገለልተኛ ምርጫ ኮሚሽን ላይ ጥቃት ሲደርስ ለሁለተኛ ጊዜ ሲሆን ጥቃቶቹ በተደጋጋሚ መፈጸማቸው በሕዝብ ዘንድ ትልቅ ሥጋትን ፈጥሯል።

የአገሪቱ ፖሊስ እንዳስታወቀው ታጣቂዎቹ በብዙ ተሽከርካሪዎች ተጭነው ወደ ከተማው ዘልቀው በመግባት ከተማዋን ከወረሯት በኋላ በምርጫ ኮሚሽኑ ላይ የተኩስ እሩምታ ከፈቱ። የተለያዩ ተቀጣጣይ ፈንጂዎችንና ቦምቦችን ወደ ሕንጻውና ተሽከሪካሪዎች በመወረወር አቃጠሏአቸው።

የናይጄሪያ ፖሊስ ቃል አቀባይ ሚካኤል አበታም እንደገለጸው፣ በወቅቱ አንድ የአገሪቱ ፖሊስ ሲገደል ከታጣቂዎቹ ሶስቱ ተገድለዋል።

“ሌላ ፖሊስ ከታጣቂዎቹ ጋር የተኩስ ልውውጥ ሲደረግ አንድ ሌላ ፖሊስ ሲቆስል ከታጣቂዎቹ ሁለቱዎቹ በቁጥጥር ስር ውለዋል›› ብሏል።

እየጨመረ የመጣው የጸጥታ ችግር በተለይም በአገሪቱ ደቡብ-ምስራቅ በተቋማት ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች የጸጥታ ኃይሎች እና የምርጫ ኮሚሽኑ በሚቀጥለው የካቲት ወር የተሳካ ምርጫ ለማካሄድ ያላቸውን አቅም ላይ ጥያቄን አስነስቷል።

## ኢራን የ23 ዓመት ወጣት በስቅሳት ቀጣች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡ በኢራን በተቀሰቀሰው ሕዝባዊ ተቃውሞ ጋር ተያይዞ የአገሪቱ መንግሥት የ23 ዓመቱ መጂደሬዛ ራሕናቫርድ የተባለውን ወጣት ፖሊስን በስለት ገድሏል በማለት በሞት መቅጣቷን ቢቢሲ ዘገበ።


ይህ ወጣት በስቅላት የተቀጣው ትናንት ሰኞ በማሽሀድ ከተማ በሕዝብ አደባባይ መሆኑን የኢራን ሚዲያዎችን ዋቢ አድርጎ ቢቢሲ አስነብቧል።

የአገሪቱ ፍርድ ቤትም ወጣቱን ‘ከፈጣሪ ጋር በመጻረር” በሚል ጥፋተኝነት ቅጣት የበየነበት ሲሆን ወጣቱ ሁለት የተጠባባቂ ሠራዊት አባላትን በስለት ወግቶ ገድሏል ሲል ዐቃቤ ሕግ ክስ መስርቶበት ነበር።

የሰብአዊ መብት ተቆርቋሪ ቡድኖች ኢራን ተቃዋሚዎችን በይስሙላ ፍርድ በስቅላት እየቀጣች ነው ሲሉ እየከሰሷት ሲሆን የወጣቱ ወላጅ እናት ፍርዱ ከተፈጸመ በኋላ ነው ስለ ልጃቸው በስቅላት መቀጣት የተነገራቸው። ከኢራን የወጡ ዘገባዎች እንደሚሉት ቤተሰቡ በቅድሚያ የመቃብር ስፍራ ቁጥር እንዲነገራቸው ተደርጓል።

ይህ ወጣት በስቅላት ሲቀጣ የሚያሳዩ ተንቀሳቃሽ ምሥሎች የተለቀቁ ሲሆን በእነዚህ ምሥሎች በአንዱ አንድ ማንነቱ የማይለይ ሰው በፍርደኛው አንገት ሥር ሸምቀቆ ገመድ ሲያጠልቅ ይታያል። ነገር ግን ምን ያህል ሰዎች በዚህ ስቅላት ቅጣት ላይ እንደተገኙ ግልጽ አይደለም። በምሥሉም ላይ በግልጽ አይታይም። ራሕናቫርድ በፍርድ ሂደቱ የራሱን ጠበቃ ለማቅረብ አልተፈቀደለትም ነበር።

ራሕናቫርድ ከሞት ቅጣቱ ቀደም ብሎ በኅዳር ወር ሁለት የተጠባባቂ ጦር ሠራዊት አባላትን በስለት በመውጋት እንደገደለ በኢራን የተለያዩ ሚዲያዎች ሲዘግቡ ነበር። ባሲጅ የሚባሉት እኚህ የተጠባባቂ ሠራዊት አባላት ኢራን ብዙውን ጊዜ ተቃውሞዎች ሲነሱ የምታሰማራቸው ወታደሮች ናቸው።


መጂደሬዛ ራሕናቫርድ

አንድ በኖርዌይ መቀመጫውን ያደረገ የኢራን የመብት ተሟጋች ድርጅት ባልደረባ የሆኑት መሐሙድ አሚሪ ሙጋዳም በትዊተር ገጻቸው እንዳሰፈሩት ራሕናቫርድ የተገደለው በግድ ያልፈጸመውን ፈጽሜያለሁ ብሎ እንዲናዘዝ ከተደረገ በኋላ ነው፤ የፍርድ ሒደቱም ገለልተኛና ፍትሐዊ አልነበረም ብለዋል።

በኢራን ትኩስ ተቃውሞ የተቀሰቀሰው አንዲት ማሻ አሚኒ የምትባል የ22 ዓመት ወጣት በግብረ ገብ ፖሊሶች ድብደባ ደርሶባት ሞታለች በሚል ነው።

አሚኒ በኢራን የግብረ ገብ ፖሊሶች በቁጥጥር ሥር ውላ የነበረው ሒጃብ በትክክል አልጠመጠምሽም በሚል ባለፈው በመስከረም ወር ነበር። ከዚያን ጊዜ የጀመረው ሕዝባዊ ተቃውሞ እስከዛሬም አላባራም።

በአሁን ጊዜ በኢራን 161 ትንንሽ ከተሞችና 31 ወረዳዎች ተቃውሞ እየተካሄደ ነው። እንዲህ ዓይነት ተቋውሞ በኢራን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ያልተለመዱ ነበሩ።

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## እማማ ጽዮን ሚካኤል አንዶም

**እፀገነት አክሊሉ**

እማማ ጽዮን ሚካኤል አንዶም፤ የመጀመሪያዋ የኢትዮጵያ ባሕላዊ አልባሳት ፋሽን ዲዛይነር፣ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል፣ የሴቶች ማኅበር፣ ማየት የተሳናቸውና ቼሻየር ሆም ምግባረ ሰናይ ድርጅቶች መስራችና የቀድሞው የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳዳር ደርግ ሊቀመንበር ጄኔራል አማን አንዶም ታላቅ እህት ናቸው። እኛም በዛሬው የባለውለታዎቻችን አምድ ላይ እኝህን የአገር ባለውለታ ልንዘክራቸው ወደናል።

የአገር ባህል አልባሳቶቻችን የእኛነታችን መገለጫ መሆናቸው እውነት ነው፤ እማማ ጽዮን አንዶምንም የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊ የባህል አልባሳት ዲዛይነር ያደረጋቸው ይኸው ነው። የአገር ባለውለታዋ እማማ ጽዮን የስራቸውን ያህል ብዙ የተነገረላቸው ባይሆኑም አገራቸውን በሚገባ አስተዋውቀው፣ ትውልድን በሙያቸው ጠቅመውና አስተምረው፣ ባህልን ማስተዋወቅ ብቻ ሳይሆን እራሳቸው ቱባ ባህል ሆነው ወደ'ማይቀርበት በመሄዳቸው ታሪካቸውን በደማቅ ቀለም ያጽፈዋል። እማማ ጽዮን አገርም ባህልም ነበሩ።

የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት የፋሺን ዲዛይነር ... እማማ ጽዮን ሚካኤል አንዶም ካርቱም ከተማ ውስጥ የተወለዱ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ የባህላዊ አልባሳት በዘመናዊ መልኩ እንዲቀርቡ ያደረጉት ጥረትም ከፍ ያለ ዋጋን ያሰጣቸዋል። የአገር ባለውለታም ናቸው። በበጎ አድራጎት ተግባራቸውም ይታወቃሉ። ሁል ጊዜም የባህል ቀሚስ የሚለብሱት እማማ ጽዮን፣ እድሜያቸው ገፍቶ እንኳ መኪናቸውን የሚያሽከረክሩት፣ ልብሳቸውን የሚያጥቡትና ሌሎች ተግባሮቻቸውን የሚያከናውኑት ... ራሳቸው እንደነበሩ የቅርብ ሰዎቻቸው ይናገራሉ። እማማ ጽዮን በ100 ዓመታቸው ነው ያረፉት። እማማ ጽዮን የጀግናውና የስመጥሩ የጦር አለቃ የጀኔራል አማን ሚካኤል አንዶም ታላቅ እህትም ነበሩ። ትግርኛ፣ አማርኛ፣ አረብኛ፣ ጣሊያንኛና እንግሊዝኛን አቀላጥፈው ይናገሩም ነበር። የአገራችን ሴቶች ከእማማ ጽዮን ሚካኤል አንዶም ጥንካሬና ስኬትን ሊማሩም ይገባል የሚል የግል አስተያየት ባክልም እወዳለሁ ።


የተለያዩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች መስራች የሆኑት እማማ ጽዮን ሚካኤል አንዶም፤ ስለ ኢትዮጵያ ባሕላዊ ፋሽን ጅማሮ፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች አመሰራረትና ስለ ታናሽ ወንድማቸው በአንድ ወቅት ከተናገሩት ውስጥም "... እኛ የተወለድነው ሱዳን ካርቱም ከተማ ነው፤ ለዚህ ዋናው ምክንያት ደግሞ አባታችን አስመራ ከተማ ላይ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ከፍ ላለ የትምህርት ሁኔታ ወደ ሱዳን ካርቱም መሄድ ስለነበረባቸው ነው። በሱዳን ካርቱምም አባታችን የከፍተኛ ትምህርታቸውን አጠናቀው ከእንግሊዞች ጋር ጥሩ ስራ በማግኘታቸው እዛው በመቆየት እኛም ተወለድን" የሚለው ይታወሳል።

የእማማ ጽዮን አባት ብዙ ቋንቋዎች መናገር የሚችሉም ስለነበሩ ለፈረንጆቹ በአስተርጓሚነትም መስራታቸውን ከህይወት ታሪካቸው እንረዳለን። የእማማ ጽዮን አንዶም አባትም ልጆቻቸውን ሱዳን ካርቱም ላይ ይውለዷቸው እንጂ ያደጉት አዲስ አበባ ከተማ ነው።

እማማ ጽዮን ስለ እናታቸውም ይህንን ብለው ነበር "... እናቴ በወቅቱ የተማረች ቢሆንም ትምህርቷ ግን ዘመናዊ ትምህርት ሳይሆን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት፤ እንዲሁም የቤት ሙያን ያካተተ ነበር። ነገር ግን እድገቷ ከስዊድኖች ጋር ስለነበር ዘርፈ ብዙ የምትባል ባለሙያ ነበረች፤ በዚህም የሁሉንም ልጆቿን ልብስ ቤት ነበር የምትሰፋው።"

የእናታቸው የልብስ ስፌት ሙያ ደግሞ እማማ ጽዮንንም ይስባቸው ስለነበር ስፌትን ገና በ12 ዓመት እድሜያቸው ይሞካከሩት ነበር፤ የአባታቸው በርካታ ቋንቋ ተናጋሪነትም ወደ'ሳቸውም ሄዶ አምስት ያህል ቋንቋዎችን አቀላጥፈው መናገርም አላቃታቸውም። በተለይም የልብስ ስፌት ሙያ ተሰጥጾአቸውን ያዩት አባታቸው ዝም ሊሏቸው አልፈለጉም፤ እናም ስጦታ ብለው የስፌት መኪና ገዝተው ሰጧቸው። በዚያም ለአሻንጉሊቶቻቸው ልብስ እየሰፉ ቀስ በቀስም የራሳቸውን ልብስ ሰፍተው እስከመልበስ የሚያደርስ ባለሙያ ሆኑ። እማማ ጽዮን በራሳቸው ይህንን ያህል ርቀት ይሂዱ እንጂ ኋላ ላይ አባታቸው አስተማሪ ቀጥረውላቸውም ልብስ ስፌት እንዲማሩ አድርገዋቸዋል።

በወቅቱ ፋሽን የሚባል ነገር ባይኖርም የአገራቸውን ጥበብ ሲያዩትም ሲለብሱትም እጅግ ያስውባቸው ስለነበር ለምን በተለያየ ፎርም አልሰራውም ብለው ተነሱ፤ በዚህም አንድ የአገር ባህል ልብስ ይሰሩና ደረቱና እጅጌው ላይ ጥበብ እያስገቡ ሌላ ገጽታን ይፈጥሩለት ያዙ፤ ይህ ሁኔታ ደግሞ ተወደደላቸው።



..... በ5 ሳንቲሜትር የተለመደውን የጥበብ አሰራር እሳቸው ወደ 50 ከዚያም ቀስ ብለው እስከ ሶስት ሜትር ርዝመት ያለው ጥበብ በመስራት ብቸኛዋና የመጀመሪያዋ ዲዛይነር ሆኑ

..... በ5 ሳንቲሜትር የተለመደውን የጥበብ አሰራር እሳቸው ወደ 50 ከዚያም ቀስ ብለው እስከ ሶስት ሜትር ርዝመት ያለው ጥበብ በመስራት ብቸኛዋና የመጀመሪያዋ ዲዛይነር ሆኑ። በወቅቱ ሴቶች በጣም ተማሩ ከተባለ 8ተኛ ክፍል ድረስ ብቻ ነበር፤ እሳቸው ግን አጋጣሚው ተመቻችቶላቸው በእንግሊዝ ትምህርት ቤት 12ኛ ክፍል የመድረስን እድል አግኝተዋል። ይህ ሁኔታ ታክሎበት በራሳቸው የሚተማመኑ፤ ለሚሰሩት ስራ ሙሉ ኃላፊነትን የሚወስዱ ልበ ሙሉ ሴትም አድርጓቸዋል። በወቅቱ ልብስ ሰፍቶ ለሌሎች ሰዎች መሸጥ በጣም ነውር የነበረ በመሆኑ እማማ ጽዮን የሰሯቸውን ልብሶች ራሳቸው ነበር የሚለብሷቸው። የጃንሆይ ልጆችና የልጅ ልጆች ደግሞ እርሳቸው የሚለብሱትን ባዩ ጊዜ "ስሪልን" እያሏቸው ይሰሩም ነበር።

በጣም የሚገርመው ነገር ግን የንጉሣውያኑ ቤተሰቦች በዚህን ያህል ስራዎቻቸውን ወደውት "ስሪልን" ይበሏቸው እንጂ ገንዘብ መቀበል ነውር ስለነበር በነጻ ነበር የሚሰጧቸው። "... በገንዘብ ሳይሆን በነጻ እሰራ ነበር። በኋላ ግን የሰው ፍላጎት እየጨመረ ሲመጣ ቤቴ መስራት ጀመርኩ፤ ግን 'ቤት መስራት አይቻልም' በመባሉ እንደምንም ሱቅ ከፍቼ መስራት ጀመርኩ"።

"......... በወቅቱ ሴት ልጅ ከቤቷ ወጥታ አደባባይ ሱቅ መቆም በራሱ አስቸጋሪ የነበረ በመሆኑ ብዙ ተቸግሬያለሁ። ግን ደግሞ የነገስታቱ ቤተሰቦች እኔ እንዳላፍ? እንድበረታታ እኔ ጋር ቁጭ ብለው ይውሉ ነበር። ከዛ በኋላ ግን ሰውም እየለመደው እኔም መስራቱ ሱስ እየሆነብኝ፤ ሱቅ ከፍቶ መቀመጥም ነውር እንዳልሆነ ተረድቼ ስራዬን መስራት ቀጠልኩ" በማለት መናገራቸው ይታወሳል።

እማማ ጽዮን ባለቤታቸውም ዲፕሎማት ስለነበሩ ለውጪው ዓለም ቅርብ ነበሩ። አጋጣሚውንም በመጠቀም ፈረንጆች ባህላዊ ልብሳችንን እንዲያውቁ የላቀ ጥረት አድርገዋል። በዚህም ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ ደረጃ አሳውቀዋታል።

እማማ ጽዮን "........ ፈረንጆች የእሱን ልብስ ዓለም ይለብሰዋል፤ የእኛ ግን ከሁሉም ይለያል። እኔ ለብሼ ሲያዩኝ ከፍ ባለ የደስታ ስሜት ውስጥ ገብተው ይገዙኛል፤ ይለብሳሉ፤ እኔም በፋሽን እሰፋለሁ" በማለት ነበር ሁኔታውን የገለፁት።

በተደጋጋሚ ቃለ ምልልስ ያደረገችላቸው የቀድሞ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ባልደረባ ስንዱ ሃይሌ ሞታቸውን ተከትሎ በማህበራዊ ገጿ ላይ እንዳሰፈረችው "... በውጭ አገር እያሉ ለቤተክርስቲያን የሚያገለግለውን፣ የሚያብለጨልጨውንና ዳር ዳሩ ዘርፍ ያለበትን ጥላ አጥልቼና ራሴ ዲዛይን ያደረኩትን የተለያየ የአገር ባህል ልብስ ለብሼ ስወጣ 'ዛሬ ደግሞ ንግሥት መስላለች' ይሉኝ ነበር" ማለታቸውን ታስታውሰናለች።

በሌላ ቃለ ምልልሷ ደግሞ «የሚገርምሽ ጥላውንም እንደ ባህሌ መገለጫ አይቼ እንጂ ከቤተክርስቲያን ውጭ እንደማይያዝ አላውቅም ነበር።» እንዳሏት አካፍላናለች። ስንዱ ስለእማማ ጽዮን ስትገልጽ ".... ሰው ወዳድ፣ ሳቂታ፣ አንደበታቸው እንደ ሕጻን ልጅ የሚጣፍጥ፣ ሁሉን ተቀባይ ናቸው። በተደጋጋሚ ላም በረት አካባቢ ወደ'ሚገኘው ቤታቸው ሄጃለሁ። ከእማማ ጽዮን ጋር የነበሩኝ ቆይታዎች ዛሬን የሆኑ ያህል እንደ ስዕል ይታዩኛል። የአገር ልብሳቸውን ለብሰው፣ ነጠላቸውን አጣፍተው ልብስ ሲሰፉ፣ «ምክንያት ካልሆነ በስተቀር የአገር ልብስ ለሥራ አይመችም የምትሉ ወጣቶች ትክክል አይደላችሁም። ይኸው እኔ ለብሼ እየሠራሁ፤ እያየሽኝ አይደል?» እያሉ በተግባር እውነታውን ሲያሳዩኝ የምመልሰው አልነበረኝም። ያኔ እንደነገሩኝ ከአገር ልብስ ውጪ በቤት ውስጥም ሆነ ውጭ ሌላ ልብስ አልለበሱም። የላቸውምም። ማየት ማመን አይደል፤ ነጭ ልብስ ብቻ የሞላውን ቁም ሳጥናቸውን ከፍተው ሲያሳዩኝ ዓይኔንም፣ አፌንም ከፍቼ ቀርቻለሁ። ከአግራሞቴ የመለሱኝ ያቺ ደስ የምትል ቀጭን ሣቃቸው ነበረች። በወቅቱ ልብስ ከሚሰፉበት ከቤቱ ጀርባ ካለው ክፍል ዳር ላይ ሸማኔዎችም አብረዋቸው እንደሚሠሩ አስጎብኝተውኛል" ትላለች።

እማማ ጽዮን፣ ቀደም ሲል ይሠሯቸው የነበሩ በሙሉ ጥበብ የተሰሩ ቀሚሶች የሚያምሩ ቢሆኑም፣ «ሙሉ ጥበብ ቀሚስ የእኛ አይደለም። ያኔ ስህተት ሠርቻለሁ። የእኛ አገር ልብሶች በነጩ ፈትል ላይ ታቹ ጥበብ የሚሠራበት ነው» ሲሉ ሌሎችም ሙሉውን ጥበብ የሆነ ቀሚስ እንዳይሠሩና ያ ከሆነ ኢትዮጵያዊ የባህላዊ ልብስ እንዳልሆነ መክረው ነበር። የአገር ልብስ ነጠላ ከሌለው ጎዶሎ ባህልም እንደሆነ ነው በተደጋጋሚ ሲገልጹ የነበረው።

እማማ ጽዮን እድሜ ልካቸውን ለጤናቸው ተስማሚ የሆነ ምግብን የሚያዘጋጁት ራሳቸው ነበሩ። በ80ዎቹ እድሜ ክልል ሆነው መኪናቸውን (ቀይዋን) ሲያሽከረክሩም ለተመለከታቸው ያስገርማሉ። የእስር ቤት ታሪካቸውንና የወንድማቸውን አገዳደል ደጋግመውም ያነሳሉ። ለንጉሡ ካባ ወስደው ሽልማት እንኳ እንዳልሰጧቸውም እንደዚያው።

እማማ ጽዮን ከፋሽን ዲዛይነርነታቸው ባሻገር የሴቶች መብት ተሟጋችም ነበሩ። ስለሴቶች ጉዳይ ብዙ ቢሉም "ሴት ዘውዷ ቤቷና ቤተሰቧ ነው። ሴት ቤት ትሰራለች። ወንድ ወጥቶ ገንዘብ ያመጣል። ቤቱን የምታስተዳድረው ሴት ናት። ነገር ግን አሁን ላይ የወንዶችን ቦታ እየያዙ ነው ሰርተውም ገንዘብ እያገኙ ነው፤ ይህ ደግሞ ሴቶች በወንድ እጅ ተዳዳሪ እንዳልሆኑ ያሳየ በመሆኑ እኩልነቱ ጥሩ ነው። ተጋግዘን ቤተሰባችንን እንምራ ማለትም ክፋት የለውም። ነገር ግን ሴቶች ውጪ ውጪውን እያሉ ቤታቸውን፣ ልጆቻቸውን መርሳት አይገባም" ሲሉም መክረው ነበር።

እማማ ጽዮን በደርግ ጊዜ ለሰባት ዓመታት በእስር ለማሳለፍ ተገደው ነበር። ".... መጀመሪያ እስር ቤት ስገባ ተደናግጬ ነበር፤ ኋላ ላይ ግን ሁሉንም ለመድኩት፤ እንደውም 20 ልጆችን አስተማርኩ፤ አሳደኩ። "... ሴቶች ወደ እስር ቤት አርግዘው ይመጣሉ፤ እዛው ይወልዳሉ፤ ሁኔታው ደግሞ ልጆችን ለመንከባከብ ምቹ አልነበረም፤ እኔም ልብሴን እየቀደድኩ ለህጻናቱ ልብስ እየሰፋሁ እያለበስኩ ቆየሁ። ይህንን የሰሙ በውጭ ያሉ ሰዎች ደግሞ ጨርቅ ይልኩልኝ ጀመር፤ ይህ ደግሞ በእስር ላይ ያሉ ሴቶችን የልብስ ስፌት ሙያ እንዳስተምር በር ከፈተልኝ። በሌላ በኩልም እስር ቤት መግባቴም ብዙ ሰው እንዳውቅ። የተለያዩ ባህርያትን እንድለምድ ስላስቻለኝ እስር ቤቱ ለእኔ ጥሩ የደስታ ቤቴ አደረኩት" በማለት ተናግረውም ነበር።

እማማ ጽዮን በእሌኒ ባርተን አማካይነት ወደ ቀይ መስቀል ስራም ገብተዋል። የመጀመሪያውን የበጎ አድርጎት ድርጅትም በማቋቋም ለብዙዎች ተምሳሌት የሆኑም ሴት ነበሩ።

ስለ እማማ ጽዮን ሚካኤል አንዶም ተናግሮ፣ በደርግ ዘመን የአገሪቱ ርዕሰ ብሔር ስለነበሩት ታናሽ ወንድማቸው፣ አማን ሚካኤል አምዶም አለመናገር ከባድ ነው።

... አማን ሚካኤል አምዶም (ኮዳ ትራሱ) በመባል የሚታወቁት የጦር ጀግና ወደ ካርቱም ለትምህርት ቢላኩም ከጣሊያን ጋር በነበረው ጦርነት ከብሪቲሽ ኮመንዌልዝ ጦር ጋር በ1933 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ። ውትድርናን የመረጡት አማን በውትድርና አገልግሎታቸው በፍጥነት በማደግ ኮርያና ኮንጎ ከመዝመት አልፎ በሀረር የሚገኘው የሶስተኛው ክፍለ ጦር (ዕዝ) አዛዥ እስከመሆን ደርሰዋል። ከሶማሌ ጋር በኦጋዴን በተደረገው ጦርነት ጀግንነታቸው የተመሰከረው አማን በወታደሮቹ "የኦጋዴኑ አንበሳ" እየተባለ ይጠሩ እንደ ነበር በሰዋሰው ድረ-ገፅ ላይ ሰፍሮ ይገኛል።

አንዳንዶች ቢቃወሙትም ... ተራማጅ የነበሩት አማን የኢትዮ-ኤርትራ አንድነት አቀንቃኝ ነበሩ። ንጉሱ የእንዳልካቸውን ካቢኔ አፍርሰው ልጅ ሚካኤል እምሩን ጠቅላይ ሚኒስትር ሲያደርጉ አማን የመከላከያ ሚኒስቴር ሆኑ። ይሁን እንጂ፣ የደርግ አባል ባይሆኑም ደርግ ሲመሰረት ከአባላቱ ጋር ግንኙነት እንደነበራቸው ይነገራል።

በኤርትራ አማጽያንና በኢትዮጵያ መንግስት መካከል የነበረው አለመግባባት በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ ይመኙ የነበሩት አማን ባለ 19 ነጥብ እቅድ አቅርበውም እንደ ነበረም ድርሳናት ያመለክታሉ።

... መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም ደርግ ንጉሱን ከስልጣን አውርዶ ስልጣን ላይ ሲወጣ አማንን የደርጉ ዋና ሊቀመንበር አድርጎ ሾመ። አማንም ከዚያ በፊት የነበረውን የኤርትራና የኢትዮጵያን ጉዳይ በሰላም የመፍታት ጥረት አጠናክሮ ገፋበት፤ በዚህ ምክንያትም የኤርትራ ጉዳይ የሚፈታው በወታደራዊ ርምጃ ብቻ ነው ብሎ ከሚያምነው መንግሥቱ ኃይለማርያም ጋር ግጭት ውስጥ ገቡ። ይህ ሁኔታ ያልተዋጠላቸው አማን በተሾሙ በሁለት ወሩ ከደርግ ዋና ሊቀመንበርነቱ ለቀቁ።

... በመጨረሻም በአሰቃቂዋ ህዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም ደርግ መኖሪያ ቤቱ ድረስ ታንክ ጭምር በመላክ የስልሳዎቹ ከፍተኛ ባለስልጣናትና ሌሎች በርካታ ወገኖች እልቂት ማሟሻ ሆኑ።

በዚህ አሰቃቂ ግድያም ምክንያት ታላቅ እህቱ እማማ ጽዮን የከፋ ሃዘን ውስጥ ገብተው እንደነበርና ከሀዘኑም አገግመው ወደ ቀድሞ ሁኔታቸው ለመመለስ ብዙ ጊዜን እንደወሰደባቸው በቅርብ የሚያውቋቸው ይናገራሉ።

እማማ ጽዮን ሚካኤል አንዶም የአገር ባለውለታ ቢሆኑም ህዳር 29 ቀን 2015 ዓ.ም አንድ ክፍለ ዘመን ሽምግለው በ100ኛ ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። ነፍሳቸው በሰላም ትረፍ።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ረቡዕ ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# በቦክስ ስፖርት ወደ ኦሊምፒክ ተሳትፎ ለመመለስ የተያዘው ውጥን

**ብርሃን ፈይሳ**

ኢትዮጵያ በታላቁ የኦሊምፒክ መድረክ በታሪክ ማህደራቸው ካሰፈረቻቸው ደማቅ ታሪኮች ጎልቶ የሚጠቀሰው የአትሌቲክስ ስፖርት ስኬታማ ነው። ኦሊምፒክ ከውጤት ባሻገር ተሳትፎም ትልቅ ቦታ ይሰጠዋልና በዚያ ረገድ ያሉ ታሪኮችን ካገላበጥን የቦክስ ስፖርት በኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ተሳትፎ ትልቅ ታሪክ አለው። ኢትዮጵያ በቦክስ ስፖርት ስምንት በሚሆኑ ኦሊምፒኮች ላይ ተካፋይ በመሆን ስፖርቱ በታላቁ መድረክ ተሳትፎ ለኢትዮጵያ ከአትሌቲክስ በመቀጠል ሁለተኛ ደረጃን ይይዛል።

የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ የቦክስ ስፖርት የተሳትፎ ታሪክ የሚጀምረው በሜክሲኮ ኦሊምፒክ ሲሆን፤ በሙኒክ፣ ሞንትሪያል፣ ሞስኮ፣ ባርሴሎና፣ አትላንታ፣ ሲድኒ፣ አቴንስ እና ቤጂንግ ኦሊምፒኮች በተከታታይ መሳተፍ ተችሏል። በዚህ ሁሉ የተሳትፎ ታሪክ ውስጥ ግን ኢትዮጵያ በውጤታማነት አገሯን ማስጠራት አልቻለችም። ይልቁንም ስፖርቱ ሲነሳ በሄዱበት አገር ስለሚጠፉ ቦክሰኞች የሚወሳው ታሪክ ያመዝናል።

በመሆኑም ኢትዮጵያ ለሶስት የኦሊምፒክ ዓመታት ከቦክስ ስፖርት ተሳትፎ መራቅ በኋላ በመጪው የፓሪስ ኦሊምፒክ ዳግም በመድረኩ ለመሳተፍ ስለሚቻልበት ሁኔታ ከወዲሁ ማሰብ ተገቢ እንደሚሆን ይታመናል። በሲድኒ ኦሊምፒክ በስፖርቱ አገራቸውን ከወከሉ 4 የቡድኑ አባላት መካከል በብቸኝነት ወደ ኢትዮጵያ የተመለሰውና በአሁኑ ወቅት በፌዴሬሽኑ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል የሆነው ኮማንደር ጸጋስላሴ አረጋይ ነው። የፌዴራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን የቡጢ ተፋላሚው ፀጋስላሴ ታዳጊ ሳለ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በርካታ የቦክስ ክለቦች መኖራቸውንና ጥቂት የማይባሉ ውድድሮች በስፖርቱ ይዘጋጁ እንደነበር ያስታውሳል። ወደስፖርቱ ከገባበት ጊዜ አንስቶ እስከ ሲድኒ ኦሊምፒክ ድረስ በተሳተፈባቸው 102 ውድድሮች ላይ 100 በሚሆኑት ላይ በማሸነፍ 26 የወርቅ ሜዳሊያ 2የብር ሜዳሊያ፤ በግብጽ በተካሄደ የዞን 5 ጨዋታ የወርቅ እንዲሁም 7ኛው መላ አፍሪካ ጨዋታ የብር ሜዳሊያ በማግኘት በሲድኒ ኦሊምፒክ ለመሳተፍ መቻሉንም ይጠቁማል።

ይህ ኦሊምፒያን እንደሚናገረው፣ ኦሊምፒክን ጨምሮ በዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ የሚደረግ ተሳትፎ ቁርጠኝነት፣ የአገር ፍቅር ስሜት እንዲሁም በርካታ አዳዲስ ባህሎችንና ልምዶችን ያስገኛል። በመሆኑም ስፖርቱ በዋናነት የሚያስፈልገው ትኩረት ነው፤ እንደ አገርም ሆነ እንደ ክለብ ከፍተኛ ገንዘብ ወጥቶባቸው ከሚከናወኑ ስፖርቶች መካከል ቦክስ የለበትም። ነገር ግን ቦክስ በጥቂት ወጪ ውጤት ሊገኝበት የሚችል ስፖርት ነው። በመሆኑም ስፖርቱ አቅም አግኝቶ ቦክሰኞቹንም ወደ ውጤታማነት እንዲመራ እንዲሁም አስፈላጊውን ነገር ለማድረግ እንደ ስራ አስፈጻሚ ስራዎች እየተከናወኑ እንደሚገኝ ያብራራል። ለዚህ ደግሞ መንግስታዊው አካልም ሆነ ስፖርቱን ማገዝ የሚችሉ ሁሉ ከጎኑ እንዲሆኑም ጥሪውን አቅርቧል።

የቦክስ ስፖርት ፌዴሬሽን የጽህፈት ቤት ተወካይ አቶ ስንታየሁ ተስፋዬ፤ የቦክስ ስፖርት ከኦሊምፒክ መራቁ ትልቅ ቁጭት እንደሆነ ይጠቁማሉ። የኢትዮጵያን የቦክስ ስፖርት ታሪክ ለማስቀጠልም ዘንድሮ አዳዲስ እንቅስቃሴዎች ተጀምረዋል። የስፖርቱ ትልቁ ችግር የነበረው የገንዘብ እና የውድድር እድል ነው። በመሆኑም በተያዘው ዓመት እንዲሁም በ2016 ዓ.ም በዚህ ረገድ የተሻለ በመሆን ስፖርቱን ለማሳደግ ፌዴሬሽኑ ጠንክሮ በመስራት ላይ እንደሚገኝ ጠቁመዋል። በተለይም ፌዴሬሽኑ ቋሚ የሆነ እና አቅም ያለው ስፖንሰር በማፈላለግ ላይ የሚገኝ ሲሆን፤ ይህ ከሆነ በዓለም አቀፍ ውድድሮች ተሳትፎ ላይ እክል የሆነውን የገንዘብ ችግር መቅረፍ ይቻላል ባይ ናቸው። ከዚህ ባሻገር ኢትዮጵያውያን ቦክሰኞች የቴክኒክ እና የአቅም ችግር የሌለባቸው እንደመሆኑ የውድድር ልምድ እንዲያገኙ በማድረግ ወደ ተሻለ ደረጃ መድረስ እንደሚቻልም እምነታቸውን ገልፀዋል።

ከዚህ ቀደም ፌዴሬሽኑ በዓለም አቀፍ ግንኙነቱ ላይ ችግሮች ሲስተዋሉ የቆዩ ሲሆን፤ ይህን በመቅረፍ በአሁኑ ወቅት መልካም በሚባል እንቅስቃሴ ላይ የሚገኝ መሆኑንም የፅህፈት ቤት ተወካዩ ያብራራሉ። የአፍሪካ ቦክስ ፎረም በቅርቡ በአዲስ አበባ ያዘጋጀው ፌዴሬሽኑ፤ በቀጣይም አዲስ አበባ ውስጥ የቦክስ ውድድሮችን፣ ጉባኤዎችን እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮችን ስለማከናወን ንግግር አድርጓል። በመሆኑም በዚህ መሰረት እንቅስቃሴው ከቀጠለ ስፖርቱ ሊያድግ የሚችልበት ወቅት ሩቅ እንደማይሆን አብራርተዋል።

ይሁንና የአገሪቷን ስፖርት በበላይነት የሚመራው የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር ከሚያደርገው ድጋፍ ጋር በተያያዘ ክፍተት መኖሩን ኃላፊው ይጠቅሳሉ። ባለፈው ዓመት በቱርክ በተካሄደው የሴቶች የቦክስ ዓለም ዋንጫ ለመሳተፍ ፌዴሬሽኑ አስፈላጊውን ዝግጅት ቢያደርግም መሳተፍ ግን አልቻለም። በተመሳሳይ ሁኔታ ዘንድሮም በስፔን በተካሄደ የታዳጊ ወጣቶች ቻምፒዮና ላይም መሳተፍ አልተቻለም። ለዚህ ዋነኛው ችግር ደግሞ በጀት ነው። በጥቂት ስፖርተኞችም ቢሆን አገርን መወከል ውጤታማ ያደርጋል፤ በመሆኑም ድጋፍ አስፈላጊ ነው። መንግስት እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት እገዛ ማድረግ ከቻለም እአአ በ2024 የፓሪስ ኦሊምፒክ ወደ መድረኩ መመለስ እንደሚችል ኃላፊው ያላቸውን ተስፋ ተናግረዋል።


## ከኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የሊዝ ፋይናንሱ አለኝታ እስከአገር መከታ

**በመሀመድ ሁሴን**

በኢትዮጵያ በአራቱም ማዕዘናት በየጊዜው ብዙ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንተርፕራይዞች በየዘርፉ ይቋቋማሉ። እነዚህ አምራች ኢንተርፕራይዞች የማህበረሰቡን ችግሮች መፍታትን፣ የጥሬ እቃ አቅርቦትን፣ የአገሪቱን የእድገት አቅጣጫ ማሳለጥን እና ወዘተ ያሉትን መሰል አላማዎች ሰንቀውና መሰረት አድርገው ሊቋቋሙ ይችላሉ፤ ይሁን እንጂ የሚጠበቅባቸውን ሚና በተገቢው ማበርከት እንዲችሉ ጥብቅ ክትትልና ድጋፍ መሻታቸው አይቀሬ ነው።

ለዚህም ነው የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት የዘርፉን ተዋናዮች አጋዥ ሆኖ ያጠናክር ዘንድ አደረጃጀቱን፣ ተግባርና ኃላፊነቱን በአዋጅ በማሻሻል ከጊዜ ወደ ጊዜ አቅሙን በማጎልበት ተደራሽ ለመሆን ጥረት በማድረግ ላይ የሚገኘው።

በተያዘው 2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመትም 660 ሚሊዮን ብር የሚሆን የስራ ማስኬጃ ብድር ለአምራች ኢንተርፕራይዞች መቅረቡን የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት በሕዳር ወር በአዳማ ከተማ ከአስፈጻሚና ባለድርሻ አካላት ጋር በነበረው ውይይት ገልጿል፡፡ ለአዳዲስና ለነባር ኢንተርፕራይዞች የሊዝ ፋይናንስ አገልግሎት በማቅረብና የስራ ማስኬጃ ብድርን በማመቻቸት ላይ እንደሚገኝም በውይይቱ ቀርቧል።

የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ አብዱልፈታ የሱፍ በመድረኩ እንደተናገሩት፤ በሩብ ዓመቱ ለአምራች ኢንተርፕራይዞች የስራ_ማስኬጃ ብድርንና የሊዝ_ፋይናንስ አገልግሎት ከማቅረብ አንጻር አመርቂ ስራ መሰራቱን በአወንታ አንስተዋል፡፡

**በዚህም በመጀመሪያው ሩብ ዓመቱ 241 ለሚሆኑ አምራች ኢንተርፕራይዞች 660 ሚሊየን ብር የሚሆን የስራ ማስኬጃ ብድር እና በሊዝ ፋይናንስ አገልግሎት ደግሞ 213 ለሚሆኑ አነስተኛና_ መካከለኛ_አምራች ኢንተርፕራይዞች 301 ሚሊዮን በላይ ብር የሚያወጡ ማምረቻ መሳሪያዎች ማሰራጨት**

በዚህም በመጀመሪያው ሩብ ዓመቱ 241 ለሚሆኑ አምራች ኢንተርፕራይዞች 660 ሚሊየን ብር የሚሆን የስራ ማስኬጃ ብድር እና በሊዝ ፋይናንስ አገልግሎት ደግሞ 213 ለሚሆኑ አነስተኛና_መካከለኛ_አምራች ኢንተርፕራይዞች 301 ሚሊዮን በላይ ብር የሚያወጡ ማምረቻ መሳሪያዎች ማሰራጨት መቻሉ አቶ አብዱልፈታህ ይገልፃሉ፡፡

419 አዳዲስ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንተርፕራይዞች በሩብ ዓመቱ መቋቋማቸውን የገለጹት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ ይህ ስራ ከዝግጅት አንጻር ጥሩ ቢሆንም በኢትዮጵያ ካለው የምርት እጥረት፣ ከስራ ፈላጊው ቁጥር አንጻር እንዲሁም ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን አስቀርቶ ወይም ቀንሶ በአገር ውስጥ አምርቶ ከመተካት አንጻር አዳዲስ ኢንተርፕራይዞችን የማቋቋምና ነባሮችን የማጠናከር ስራ በትኩረት መስራት እንዳለበትም አሳስበዋል፡፡

በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች የሚታየውን የአፈጻጸም ልዩነት ወደ ተቀራራቢነት ለማምጣት በትኩረት ይሰራል ያሉት አቶ አብዱልፈታ፤ በቀጣይ የክትትልና ድጋፍ ስራውን በማጠናከርና ዝቅተኛ አፈጻጸም ያላቸውን ስራዎች በመለየት ከዘርፉ አስፈጻሚዎችና ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት እንደሚያስፈልግ ይናገራሉ፡፡

በመድረኩ በነባር አምራች ኢንተርፕራይዞች ክትትልና ድጋፍ እንዲሁም አዳዲስ ኢንተርፕራይዞችን በማቋቋም የተሻለ ልምድና ተሞክሮ ያላቸው ክልሎች ልምድና ተሞክሯቸውን አካፍለዋል። የአማራ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ተፈሪ ታረቀኝ እንዳሉት፤ አምራች ኢንተርፕራይዞች ወደ ውጭ ገበያ መቅረብ በሚችሉ ምርቶች ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት ይገባል፡፡

ይሄን ማድረግ ከተቻለና በተገቢው አምራቾች ድጋፍና ክትትል ከተደረገላቸው የውጭ ምንዛሪ እጥረት[illegible] በመቀነስ፣ በአገር ውስጥ ተኪ ምርቶችን በስፋት በማቅረብ[illegible] የወጭና ገቢ ምርቶችን ወደ ማመጣጠን ይሄዳሉ። ይህ[illegible] ሲሆን በሂደት የአገሪቱ ኢኮኖሚ መሰረት እየጣለ በቀላሉ[illegible] እንዳይዋዥቅ ይረዳል ብለዋል። በተመሳሳይ አምራች[illegible] ኢንተርፕራይዞችን ከአነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ[illegible] በሚል የሚመዘኑበት መስፈርት ወጥ የሆነ አገራዊ ነባራዊ[illegible] መጠሪያና መስፈሪያ ሊኖራቸው እንደሚገባም አቶ ተፈሪ[illegible] አሳስበዋል።

በአጠቃላይ የአምራች ኢንተርፕራይዝ ዘርፍ[illegible] ተወዳዳሪነትን በማሳደግ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር[illegible] እንዲፋጠን ማድረግ አስፈላጊ ነው።

በመሆኑም ለአምራች ኢንተርፕራይዞች ችግር[illegible] ፈቺ የአቅም ግንባታ፣ የፋይናንስ፣ የማምረቻ መሳሪያ፣ የቴክኖሎጂ፣ የምክር አገልግሎት፣ የማምረቻ ቦታና[illegible] መሰረተ-ልማት፣ የግብዓትና የገበያ ትስስር ድጋፎች[illegible] በመስጠት ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን[illegible] የማስፋፋትና የማሸጋገር ተልዕኮን እውን የማድረጉ ተግባር[illegible] ለይደር የሚቆይ አይደለም።

የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማትም ይሄን አላማ[illegible] እውን ለማድረግ ታስቦ የበቀለ መስርያ ቤት እንደመሆኑ[illegible] በየጊዜው አቅሙን እያጎለበተ እና ተልኮዎቹን ከአገሪቱ[illegible] የለውጥ አቅጣጫዎች ጋር በማጣጣም የስራ እድል[illegible] ፈጠራን በማስፋት ዜጎችን በተለይም ወጣቶችን በሊዝ[illegible] ፋይናንስ አገልግሎት እና በስራ ማስኬጃ ብድር እየደገፈ[illegible] ይገኛል። ለዚህ አላማው ስኬትም ይረዳ ዘንድ አደረጃጀት፣[illegible] ስልጣንና ተግባሩን ለመወሰን ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ በሩብ[illegible] ዓመቱ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ መጽደቁ ለዘርፉ[illegible] የበለጠ ትኩረት እንዲሰጠው የሚያደርግ አወንታዊ[illegible] ተግባር ነው፡፡

ቴሌግራም፡t.me/ethiopianenterprisedevelopment
ፌስቡክ፡ www.facebook.com/ethiopianenterprisedevelopment